

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሦስቱን ወጣቶች ከእሳት ነበልባል እንዳዳናቸው።

# ትንሣኤ



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በላሞች በረት በተወለደ ጊዜ
እህያና ላም በትንፋሻቸው ሲያሞቁት ።

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማ ው ጫ

## አርእስት ፤

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| የክርስቶስ ልደት ለዓለም ደስታና ደኅንነት | ፪ |
| የቅዱስ ገብርኤል ድንቅ ሥራ በሃያኛው ምዕት ዓመት | ፬ |
| መላእክትና ሰዎች አንድ መንጋ ሆኑ | ፮ |
| የቅዱስ ሲኖዶስ ትርጉምና ዓላማ | ፰ |
| የመጀመሪያ ተጠሪ ሐዋርያ | ፱ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፲ |
| የቤተ ሰብ ዓምድ | ፲፪ |
| የተባረከ ልደት | ፲፬ |
| ገዳም መርጃ ፤ ወይስ መረጃ ፤ | ፲፮ |
| የግብርና በረከት | ፲፯ |
| ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብ | ፲፰ |
| ድንግል በቤተ ልሔም | ፲፱ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፳፩ |
| ትምህርተ ግዕዝ | ፳፪ |
| ዜና ሊቃውንት | ፳፫ |
| መልካሙን የምሥራች እንናገር | ፳፬ |

# ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

እስቀድሜ እንኳን ለአዲሱ ዘመን ከድርጅቱ ሠራተኞች ጋር አደረስዎ እያልኩ መንፈሳዊ ምኞቴን እገልጻለሁ ከዚህ ቀጥየ ለማቀርበው ጥያቄ በቂ መልስ እንደማገኝ እተማመናለሁ

፩ኛ/ ጥያቄዬ ቅዱስ ፓትርያርኩ ለዘመን መለወጫ ለገናና ለትንሣኤ በዓል በራዲዮና በቴሌቭዥን ንግግር ከማድረጋቸው በፊት በዓሉን የሚመለከት ጥቅስ በዜማ ተሰምቶ ቃለ ምዕዳኑ ለምን አይሰማም ?

፪ኛ በክብረ በዓል ቀን ታቦቱ ወጥቶ ሲቆም ጳጳሳቱና አንዳንድ ሰዎች ለምን ይቀመጣሉ?የድካም ነው? ወይስ ደንብ አለ?

፫ኛ/ «ሙሴ ሙሴ ፍታሕ ቶታነ አሣዕኒከ እምእገሪከ እስመ ዘትከይዳ ምድር ቅድስት ይእቲ» እያለ እስከ መቅደስ በዜማ ለምን ይገባል?

፬ኛ/ በአዲስ አበባ ከተማ ጃንጥላና አልባሳት ከገቢያ ተገዝተው እንደገናበነጋዴዎች እጅ ወደገቢያ ይመለሳሉ በገጠር ላሉ አብያተ ክርስቲያናት በርዳታ መልክ ለምን እንዲሰጡ አይደረገም ?

ከዚህ በተረፈ ትንሣኤ መጽሔት የምታወጣው ቃል በውነቱ እንደማር የሚጣፍጥ ስለሆነ በዚሁ ግልጋሎት ጸንተህ እንኳን ለሃያኛው ዓምት አደረሰህ እያልኩ ደስታየን እገልጻለሁ ፤

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሣን ከበደ

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሣን ከበደ የመጽሔታችን ተከታታይ በመሆን ስለአቀረቡልን መንፈሳዊ ሰላምታና ጥያቄ ከልብ እናመሰግናለን ወደፊትም መጽሔታችንን እየተከታተሉ በማንበብ አንዳንድ አሳቦችን እንደሚለግሱን ተስፋ እናደርጋለን።

ከዚህ ቀጥሎ ስለአቀረቧቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ፩ኛ ቅዱስ ፓትርያርኩ ቢታታላቅ በዓላት በዘመን መለወጫ ፤ በልደትና በትንሣኤ ቃለ ምዕዳን ከማድረጋቸው በፊት በዓሉን የሚመለከት ጥቅስ በዜማ እንዲሰማ ያቀረቡት ጥያቄ እጅግ በጣም የሚደገፍ ነው ችግሩ ግን የሰዓት እጥረት ነው የሚፈቀደው ሰዓት አጠር ስለሚል መዝሙሩ ቢጨመርበት ደግሞ እጅግ በጣም ያጥራል ስለዚህ ጸሎተ ምዕዳኑ ጊዜ ያንሠዋል በማለት ይሆናል ።

፪ኛ አባቶች የሚያድሩት በጸሎት በስግደት በአስተብቁዖት ሲሆን በጸሎተ ቅዳሴም ተገኝተው ጸሎቱን ይመራሉ ይባርካሉ ታቦቱ ወጥቶ ከቆመ በኋላም ቤታቦቱ ፊት የካህናቱ ሽብሸባ የወጣቶቹ መዝሙርና ሌላም ብዙ ዝግጅቶች ስለሚፈጸሙ አባቶችን እጅግ በጣም ይደክማቸዋል ስለዚህ ትንሽ ከድካም ተንፈስ ለማለት ይቀመጡ እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ታቦት ቆሞ ተቀመጡ የሚል ቃል አልተጻፈም፤

፫ኛ/ዜማ ተዜምቶ ወደቤተ መቅደስ መግባት ክልክል መሆኑን እየተጠየቅን በዚሁ መጽሔታችን ደጋግመን መልስ ሰጥተናል መልሱም ዜማ ተዜምቶ ወደቤተ መቅደስ አይገባም የሚል ነው መረጃም ቢያስፈልግ አራዘፀ-፫-፭ መመልከት ይበቃል።

ስለዚህ የጠያቂውን መልስ ለማጠቃለል በገጠር ላሉ አብያተ ክርስቲያናትከምዕመናን በስተቀር ሌላ ረዳት ስለሌላቸው ምእመናን በተቻላቸው መጠን ንዋያተ ቅዱሳቱን እየገዙ በማቅረብ ቤተ ክርስቲያንን የመርዳት ግዴታ እንዳለባቸው ሊያውቁት ይገባል ።

## ማሳሰቢያ

ትንሣኤ መጽሔታችንን በየወሩ እየተከታተላችሁ የምታነቡ ደንበኞቻችን ! በዚሁ መጽሔታችን እያሳተምን ስለምናወጣቸው መንፈሳውያን ትምህርቶች አንዳንድ ቅን አመለካከትና አስተሳሰብ ቢኖራችሁ በደብዳቤ ግለጹልን ።

አሳባችሁን በደስታ እንቀበላለን ፤ የምታቀርቧቸው መንፈሳውያን አስተያየቶችና ቅን የሆኑ አስተሳሰቦችም ለዝግጅታችን ይረዱናል ።

የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
የስልክ ቁ. 116616
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ።
አ.አ.



www.ethiopianorthodox.org

## (ርእሰ አንቀጽ)

# የክርስቶስ ልደት ለዓለም ደስታና ደኅንነት

«እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ ዛሬ በዳዊት ከተማ
መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል ። ሉቃ ፪፡፲/ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዞ
የመዳን ተስፋው ለመነመነ ፤ ዛሬ ወይም ነገ እሞታለሁ በማለት ይጨነቅ ለነበረ በሽተኛ መድኃኒት
ተገኘልህ ነገ ትድናለህ ቢሉት እውነት ሊመስለው አይችል ይሆናል ። ግን የመድኃኒቱ መገኘት እውነት
ይሆንና መድኃኒቱን ተቀብሎ ከበሽታው ሲፈወስና ከሞት ሲተርፍ ደስታው የበዛ ይሆናል ። ባለመድኃ
ኒቱንም ያመሰግናል ከቻለም ወረታውን ለመክፈል ይሞክር ይሆናል ።

የመጀመሪያው ሰው የፈጣሪውን ሕግ በመተላለፉ ምክንያት ዓለም በመላ ሰላምንና ደስታን አጥቶ
በጭንቀትና በጥርጥር ወድቆ ነበር ሰው በተድላና በደስታ በሰላምና በፍቅር በኅብረት እንዲኖርበት የተ
ፈጠረው ዓለም በሰዎች ክፋት የመከራና የሥቃይ የኀዘንና የትካዜ የጠብና የመለያየት ዓለም ሆነ ሰዎች
ከአምላካቸው በተሰጣቸው ጸጋ ከብረውና ተደስተው መኖራቸውን አጡ፤ ድኅነትና በሽታ ቅኝ አገዛ
ዝና የዘር ልዩነት ግፍዕና ዓመፅ በዓለም ሰፈነ ።

ዓለም በዚህ አሰቃቂ ሁኔታ ላይ ሳለ «ለድሆች የምሥራች እነግር ዘንድ የእግዚአብሔር
መንፈስ በላዩ ነው ለታሠሩት መፈታትን ለዕውሮች ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ
ዘንድ ልባቸው የተሠበረውንም እፈውስ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን (የመዳን) ዓመት እሰብክ ዘንድ
ልኮኛል» የሚል ደስታን ነፃነትንና ሰላምን የሚያውጅ የምሥራች ተስማ ኢሳ- ፷፩፡፩—፪ ። ይህን የም
ሥራች የሰሙ ሁሉ የተወደደችውን የመዳን ዓመት በተስፋ ይጠባበቁ ነበር ከዚያች የደስታና የመዳን
ቀን ለመድረስ ስለሚናፍቁ አንዱ ቀን እንደ አንድ ሺህ ቀን አንድዋ ሌሊት እንደ አንድ ሺህ ሌሊት ይሆ
ንባቸው ነበር አዎ የችግርና የመከራ ቀን ቶሎ አይመሽም ሌሊቱም ቶሎ አይነጋም የመከራ ሌሊት ነውና።

በጠላት እጅ ተይዞ ነፃነቱን አጥቶ በባዕድ አገዛዝ ለወደቀ ሕዝብ ከነፃነት፤ በጤና ጉድለት ምክ
ንያት በደዌ ተይዞ ለሚሰቃይ ከጤንነትና የሰላም እንቅልፍ ከማግኘት የበለጠ የሚናፍቀው የለም ።
በዓለም ሰላምና ደስታ ። ነፃነትና እኩልነት፤ የአእምሮ ጤንነትና የሕሊና ዕረፍት ጠፍቶ ሞትና ኃጢአት
ኀዘንና ጭንቀት በበዛበት ዘመን የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ተወለደ ። «ለእግዚአብሔር በሰማያት ምስ
ጋና ይሁን በምድርም ለሰው ዘር ሰላም ተሰጠ » የሚለውን መዝሙር መላእክትና ሰዎች በአንድነት
ዘመሩ ። የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት አጥቶት የነበረውን ነፃነትና ሰላም በክርስቶስ ልደት
አገኘ ኃዘኑና ጭንቀቱ ተወገደለት « ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የመሥራች» የሚለው ብሥ
ራት በመላእክት ለሰዎች ተነገረ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ዕርቅ ሆነ ሰላም ተፈጠረ ሰው
ከፈጣሪው ጋር በመታረቁ በሰማይና በምድር የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ ተደሰቱ በኃጢአት ምክንያት
በጨለማ ተውጦ ለነበረው ዓለም ብርሃን ወጣለት ። የክርስቶስ ልደት በድንቁርና ለነበሩ ዕውቀትን
በኃጢአት ለነበሩ ሥርየትን በሞት ጥላ ለነበሩ ደኅንነትን በግዞት ለነበሩ ነፃነትን አስጥቶአል ።

እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ በመወለዱ ያልተደሰተ ፍጥረት የለም ፤ ምክንያቱም በሰዎች
በደል ምክንያት ተጐሳቁሎ የነበረው ዓለም በክርስቶስ ልደት እንደሚታደስ ፍጥረት ሁሉ በተስፋ ይጠባ
በቅ ነበርና ነው ። «የተወደደችው የመዳን ዓመት» ከተባለችው ከክርስቶስ ዕለተ ልደት አስቀድሞ
ኀዘንና ችግር ያልነበረበት ቤትና መንደር አልነበረም ። በዘር በሚተላለፍ የኃጢአት ደዌ ያልተበከለ ኀብ
ረተሰብ አልነበረም ሁሉ በሽተኛ ሁሉ ችግረኛ ሁሉ ኃዘንተኛ ሆኖ በየደጁ ኀዘን ነበር ። ይህን ሁሉ የሰ
ዎች ችግር ተመለከተና እግዚአብሔር ርኅራኄ ሊያደርግላቸው ወደ ጨኸታቸውን ሰማ ኀዘናቸውንና



ችግራቸውን ለማስወገድ ፈቃዱ ወደ ሰው ልጆች አዘነበለ ። ሰው የሚሻውንና የሚፈልገውን በማወቅ
የሰዎችን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ ። አንድን ችግረኛ ለመርዳት ከታሰበ ወደ ችግረኛው ቀረብ ብሎ ችግ
ሩን መረዳት ያስፈልጋልና። ችግራቸውንና ፍላጐታቸውን አውቆ ባሕርያቸውን ገንዘብ ካደረገ በኋላ በየ
መንደሮቻቸው እየተዘዋወረ በሽተኞችን ፈወሰ ፤ የታረዙትን አለበሰ ፤ የተራቡትን አጠገበ ፤ የተጠሙትን
አረካ ፤ ዐይን ለሌለው ዓይን፤ እጅና እግር ለሌለው እጅና እግር በመስጠት ፍጹም ቸርነቱንና ፍጹም ፍቅ
ሩን ለሰው ልጆች ገለጠ ከሁሉ በላይ የሆነ የባሕርይ አምላክ ሲሆን እጅግ የደኸዩትንና በሰው ዘንድ የተ
ናቁትን አልናቀም ። በሽተኞችንም አልተጸየፈም ነፍስ ሁሉ በእርሱ ዘንድ የከበረ ነውና።እርሱ ሁልጊዜ
ክቡር ሲሆን ለሰዎች በማዘን ራሱን ዝቅ አድርጎ ትሑት ሥጋን ተዋሐደ የሰዎችን ኃዘን ለማስወገድና
ለእነርሱ ደስታን ለመስጠት ሥጋን ተዋሕዶ ተወለደ ። እርሱ በሥጋ በመወለዱ ዓለም ከውድቀተ ኃጢ
አት ተነሣ ። ሰዎች የዘለዓለም ተድላ ነፍስን ያገኙ ዘንድ አምላክ በሰዎች ዓመፅና ተንኮል ወደዚህ ዓለም
መጣ «በመምጣቱም ፍጥረት ሁሉ ተደሰተ» ኤፍሬም ፩፡፱ የእርሱም በሥጋ መገለጡ የዓለሙ ተሐ
ድሶ ሆነ ።

እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱና ከቅድስት ድንግል ተወልዶ የሰ
ውን ባሕርይ ገንዘብ በማድረጉ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ለመባል በቁ ። በጠላት በዲያብሎስ ምክር
በተሳሳቱ ጊዜ አጥተውት የነበረውን የልጅነት መዓርግ መልሰው አገኙ ። የዓለሙም ሁሉ ታላቅ
ደስታ የተባለ ይህ ነው ። «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ
ሰጠን እዩ እንዲሁም ነን ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን» ፩ኛ ዮሐ ፩—፪

ለሰው የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ ከመሆንና ከነፃነት የበለጠ ክብር ወይም ደስታ አይኖረውም
ለሰው የእግዚአብሔር ... ራሱን ዝቅ አድርጎ ለተወለደው የሰውን
ታዲያ ለሰው ደስታንና ሰላምን ነፃነትንና ክብርን ይሰጥ ዘንድ ራሱን ዝቅ አድርጎ ለተወለደው የሰውን
ውርደትና የዓለምን ጉስቁልና ሳልተጸየፈ ለእርሱ የሚከፈለው ዋጋ ምንድን ነው፤ የልደቱስ በዓል በምን
ሁኔታ ሊከበር ይገባዋል ? ተብሎ የተጠየቀ እንደሆነ እርሱ እግዚአብሔር ወልድ በኃጢአት የተጐሳ
ቆለውንና የተበላሸውን ዓለም ለማደስ ራሱን ዝቅ አድርጎ በትሕትና መጥቶ ከጉስቁልናው አድሶ እን
ዳስደሰተው ሁሉ ዛሬም ሰዎች የተቸገሩትን በመርዳት ያዘኑትን በማጽናናት በዓለ ልደትን ቢያከብሩ
ደስታቸው ፍጹም ይሆናል ።

ስለዚህ የጌታችንና የመድኃኒታችንን የልደት በዓል ስናከብር እርስ በርሳችን መገባበዝና ስጦታ
መለዋወጥ ብቻ ሳይሆን በገንዘባችን የተቸገሩትን በመርዳት ልባችን በንጹሕ እምነት አጽንተን ለበዓለ
ልደቱ የእጅ መንሻ አድርገን ማቅረብ ይፈለግብናል ። የጌታችን ልደት ለእኛም የነፍሳችን ልደት ነው
በነፍሳችን በሲኦል ከመጣል በእግረ ሰይጣን ከመረገጥ ነፃ የወጣንበት መንፈሳዊ በዓል ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስ ገብርኤል ድንቅ ሥራ በሐያኛው ምዕት ዓመት

ቅዱስ ገብርኤል ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ነው ስለ ድንቅ ሥራ፤ስለ መልካም አገልግሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ በየጊዜው እየተላከ ለኃጥአን ምሕረትን የሚያመጣ ፤ ለጻድቃንም የምሥራችን ያበስር የነበረ ቅዱስ ገብርኤል መሆኑን ታላቁ መጽሐፍ አልፎ አልፎ በየገጹ ጠቅሶታል ። ከድንቅ ሥራውም የተነሳ በብሉይ ዘመን በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ ተወዳጅነትንና ተፈሪነትን ያተረፈ መልአክ ሆኖ እናገኘዋለን። በሐያኛው ምዕት ዓመትም በሚኖረው ሕዝብ መካከል በትንሹም በትልቁም ዘንድ በድንቅ ሥራው በረዳትነቱ፤በሰሚነቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ እየተላከ ስለትን በመፈጸሙና አገልግሎትን በመስጠቱ የመታወቅን፤የመደነቅን፤የመወደድን ፤ የመፈራትን ከፍተኛ ደረጃ ይዞ የሚረዳ ታማኝ የሰላም መልአክ ነው ።

ይህም በመሆኑ «ገብርኤልን የማይጠምቅ ሞትን የማያውቅ ሰው አይገኝም» እየተባለ ይተረክለታል ፤ ይህም ማለት በየዓመቱ የቅዱስ ገብርኤልን በዓል የማይዘክር ክርስቲያን አይገኝም ለማለት ነው። ወደ አባባሉ ያተኮርን እንደሆነ ቅዱስ ገብርኤል ያደረገው ድንቅ ሥራና የፈጸመው አገልግሎት ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ዘመን ይልቅ በሐያኛው ምዕት ዓመት እጥፍ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ይህንንም ለማመዛዘን ቢፈለግ ቅዱስ ገብርኤል በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን የፈጸማቸውን ድንቅ ሥራዎች መረጃ እንዲሆኑ ቀጥለን እንጠቅሳቸዋለን ፩ኛ/ ናቡከደነጾር ሶስቱን ወጣቶች ወደእቶን እሳት ባስጣላቸው ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ በኃይል ይነድ የነበረውን እሳት እንደ በረዶ አቀዝቅዞላቸዋል ። ናቡከደነጾርም በገዛ ሥራው እየተደነቀ ታስረው እሳት ውስጥ የተጨመሩት ሶስት ነበሩ እሁን ግን በእሳት መካከል የሚመላለሱ ሰዎችን አራት አያለሁ ምንም አላቆሰላቸውም የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል ብሎ መለሰ ፤ ይህም ቅዱስ ገብርኤል ነው ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ፫ ከቁጥር ፳፭—፳፯ ፤

ይህም የሚያሳየን ቅዱስ ገብርኤል የፈጸመውን ድንቅ ሥራ ብቻ ሳይሆን ሦስቱ ወጣቶችም የእግዚአብሔር አምልኮት በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ ስላደረጉ በሕይወታቸው ቀርቶ ልብሳቸው እንኳ ሳይጠቁር ጥላሸት ሳያርፍበት መገኘቱ የእግዚአብሔር ኃይል በነሱ ላይ አድሮ መሥራቱን ይገልጽልናል። ይህም ሁኔታ በየጊዜው እግዚአብሔርን እምነው ለሚሠሩ ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብርኤልን እየላከ ከልዩ ልዩ መከራና ስቃይ እንደሚያድናቸው ይህ ድንቅ ሥራ ምስክር ነው።

፪ኛ/ ከክርስቶስ ልደት በፊት በስድስተኛው መቶ ዓመት የነበረው ነቢዩ ዳንኤል በፋርስ ተማርኮ ሳለ እራሱና ወገኖቹ በስደት በነበሩበት ጊዜ ስለሚደርስባቸው ግፍና ሰቆቃው ሲያዝን ሱባኤም ገብቶ በሚጸልይበት ወቅት ከእግዚአብሔር የተላከው ቅዱስ ገብርኤል ስላደረገለት እርዳታ ስለ ድንቅ ሥራ ስለገለጠለት ጥበብ እንደሚከተለው መስክሮለታል ።

«ገናም በጸሎት ስናገር አስቀድሜ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ፤ በማታም መሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ አስተማረኝም ተናገረኝም እንዲህም አለ ዳንኤል ሆይ ! ጥበብንና] ማስተዋልን እሰጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ። አንተ እጅግ የተወደድህ ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትእዛዝ ወጥቶአል እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ አሁንም ነገሩን መርምር ራእዩንም አስተውል» ትንቢተ ዳንኤል ምራፍ ፱ ከቁጥር ፳፩—፳፫

ከእንዲህ ያለው ድርጊት ክርስቲያኖች ሁሉ ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።ዳንኤል ይህን ሁሉ ሊያገኝ የቻለው እየጸለየ እግዚአብሔርን በመለመኑ ነው። ማንኛውም ክርስቲያን እንደሱ በእውነት እየጸለየ እግዚአብሔርን ከለመነ ገብርኤል እያሰበ ወደሱ ይመጣል በራእይም ተገልጦ ያነጋግረዋል ሕይወቱንም በመንፈስ ይዳስሰዋል ። መንፈሳዊ እውቀትንና ማስተዋልን ይሰጠዋል ፤ ኀዘኑንም ሆነ ችግሩን ያቃልልለታል ። ሰዎችን ለማገልገል በእግዚአብሔር የሚላክ የምሕረት መልክተኛ ነውና ።

ሶስተኛ ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስና ለባለቤቱ ለኤልሳቤጥ የፈጸመው ድንቅ ሥራ ነው ይኸውም ሁለቱ መካን ሆነው ካረጁ በኋላ የሚከተለውን የምስራች ቃል ለዘካርያስ አበሰረው «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሐልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፩ ከቁጥር ፲፫—፲፬ ፡ልጅ መውለድ የተሳናቸው መካኖች ሁሉ ልጅ እንዲወልዱ ለቅዱስ ገብርኤል የሚሳሉት ይህን መሠረት በማድረግ ነው ።

ይህም በመሆኑ ከላይ ስማቸው ለተጠቀሰው ቅዱሳን ቅዱስ ገብርኤል የፈጸማቸው ድንቅ ሥራዎች በየጊዜው ከሚነሣው ትውልድ ጋር ዘመናትን አቋርጠው በመንፈስ እየተጓዙ በክርስቲያኖችና በቅዱስ ገብርኤል መካከል ያለውን ወዳጅነት እንደ ፋና ሲያበሩት ይኖራሉ ። ።

ሌላው አንዳንድ አማኞች ለወንጌል መስፋፋት ለቤተክርስቲያን እድገት መስቀሉን ተሸክመው ሲጓዙ በእሳት፤ በስለት፤ በእስራት ይፈተናሉ ለእራዊት ይጣላሉ። በዚህ ጊዜ እሳቱን ስለቱን እንዲቀዘቅዝላቸው በእስራት ሳሉ ኃይል እንዲያገኙ አራዊቱን ለማዳ እንዲያደርግላቸው ከእግዚአብሔር የሚላክላቸው ቅዱስ ገብርኤል መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክርልታል ። እንዲህ ያለውም ድንቅ ሥራ ክርስቲያኖችን እንደ ደወል ድምፅ ለመልካም ሥራ ይቀሰቅሳቸዋል ። ገብርኤል የፈጸማቸው እነዚህ ሥራዎች አንድ ጊዜ የተፈጸሙ እንጂ በየዓመቱ ሲፈጸሙ አይኖሩም ።

በሐያኛው ምዕት ዓመት ግን በየዓመቱ ታህሣሥ ፲፱ ቀን በኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት በቅዱስ ገብርኤል ስም የታነፁ ከ፫ሺ በላይ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ። በነዚህ ሁሉ እየተገኙ የሚሳለሙት ክርስቲያኖች ሁሉ በቅዱስ ገብርኤል ፤ተፈጸመላቸውን ድንቅ ሥራና አዳዲስ ተአምር ሲያቀርቡ መስማትና ማየት ዕጹብ ድንቅ ከማለት በቀር ሌላ መልስ አይገኝለትም ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የወንጌል መምህራን ተዘዋውረው ያስተማሩባቸውን በጣም ታዋቂ የሆኑትን አራት የገብርኤል አብያተ ክርስቲያኖች ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን።

አንደኛ በአዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ገብርኤል ሁለተኛ በወላይታ ደልቦ ቅ/ ገብርኤል ሦስተኛ በጋሙጎፋ ኤሊ. ገብርኤል በነዚህ በሶስቱ የተሳላሚው ብዛት የስለቱ አገባብ ማለት በገንዘብ በእጣን፤በጧፍ፤ በሻማ፤ በጃንጥላ በከብት አገባብ በኩል ተመሳሳይ ሲሆን በአንዳንድ በኩል የሚለያዩበት አለ። ለምሳሌ ኤሊ. ገብርኤል ቅቤ ፤ ቡልኮ ፍራፍሬዎችና የኮባ ችግኝ የቀጨማ ጉዝጓዝ በብዛት ሲገቡ ደልቦ ገብርኤል ደግሞ ማንኛውም ሰው ሌላ ስለት ቢይዝም እንደ ባህል ሆኖ ድንጋይ በራሱ ላይ ተሸክሞ ይመጣና ከዚያው ይጥለዋል ድንጋዩም በብዛት ይከመራል እንቁላል ዶሮ ማርና ቅቤ በብዛት ይገባል።

አራተኛው ደግሞ በሐረርጌ ክፍለ ሀገር የሚገኘው ቁልቢ ገብርኤል ነው ከአዲስ አበባ ከተማ ፬፻፳፪ ኪሎ ሜትር ተጉዞ በወበራ አውራጃ የድንቅ ሥራ ፈጻሚ የሆነው የቅዱስ ገብርኤል በዓል በየዓመቱ ታህሣሥ ፲፱ ቀን ከአስራራቱ ክፍላተ አገር በተሰበሰቡና በውጭ ሀገሮች ዜጎች ተከብሮ የሚውለው ነው የወንጌል መምህራኑ እንደተመለከቱት ወደዚህ ቅዱስ ቦታ የሚመጣው ተሳላሚ ሁሉ ተራራ ሸለቆ የሀገር እርቀት የሃይማኖት ልዩነት አቅምና ገንዘብ ሳያግደው በማየታቸው የቅዱስ ገብርኤልን ተራዳኢነትና ሰሚነት ምን ያህል እንደሆነ አድንቀዋል። በተጨማሪም አንዱ ለሌላው የሚያደረገውን ሰብአዊ ርኅራኄና የሚያሳየውን ፍቅር በማየታቸው በቅዱስ ገብርኤል ድንቅ ሥራ ተገርመዋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ዓመት ዲዳ ሆኘ ስኖር ተናገርኩ እንደ ትኋን በአልጋ ላይ ተጣብቄ ስኖር ከበሽታዬ ድኘ መጣሁ ጆሮቸ ደንቁረው ስኖር ለመስማት ቻልኩኝ፤በሲጃራ አመል ተይዤ ስኖር ከእንዲህ ያለው መጥፎ ጠባይ ተላቀኩ፤ በመጠጥ ሰካራም ወፈፌ ሆኘ ስኖር ይሄው ገብርኤል ገላገለኝ እያሉ ስለ ገብርኤል ድንቅ ሥራ የሚናገሩ ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ ነው በጠቅላላው ሁሉም እንደተሳለው በጉልበቱ ተንበርክኮ መዳሀ ከወገቡ በላይ እራቁቱን ሆኖ መሄድ ድንጋይ ተሸክሞ ቤተ ክርስቲያኑን መዞር ሴቶች በስዕለት የወለዱዋቸውን ልጆች ትናንሾቹን ታቅፈው ከፍ ያሉትን በእግራቸው ድክ ድክ እያደረጉ ማዞር ከድሬዳዋና ከሐረር ከተማ ከ፸፭ ኪሎ ሜትር ያላነሰ መንገድ በእግር በመጓዝ የቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያጣበበው የሰው ዓይነትና ብዛት ምግብ ተመግቦ የሚያድር መምሰሉ ቀርቶ ወደባዓቱ ለመመለስ እንኳ መንገድ የሚያገኝ አይመስልም ።

በዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተሳይ ሲጠይቁት በብዙ ዓይነት መልክ እንደ ተሳለና ስለቱም እንደደረሰለት ይናገራል አድናቆቱም እጅግ ነው ትርኢቱም ብዙ ነው በዚህ አኳኋን በየዓመቱ ታህሣሥ ፲፱ ቀን የእግዚአብሔር መልክተኛ የሆነው ቅዱስ ገብርኤል የፈጸመው ድንቅ ሥራና ተአምር ቢጻፍ የመጽሔታችን ዓምድ ባልቻለውም ነበር ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ





www.ethiopianorthodox.org

# «መላእክትና ሰዎች አንድ መንጋ ሆኑ»

መንጋ የሚለው ቃል ሰዎችንና መላእክትን እንስሳትንና አራዊትን አዕዋፍንና የመሳሰሉትንም አጠቃሎ የሚገልጽ ቃል ነው ይህ ብቻሳይሆን አንድ ዓይነት ተፈጥሮ ያላቸውም ቢሆኑ በቁጥር በርከት ሲሉ መንጋ እየተባሉ ይጠራሉ፤ በሌላም በኩል የጅብ የወፍ የአንበሳ የአይጥ ወዘተ መንጋ እየተባለ ይነገራል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ባስተማረበት ክፍለ ዘመን ግን እራሱን በጠባቂ ቃሉን የሚከተሉትን በመንጋ እየመሰለ አስተምሯል ።

ወንጌላዊው ሉቃ፤ በጻፈው ወንጌል ምዕ-፲፪ ቁ- ፴፪ ላይ « አንተ ታናሽ መንጋ መንግሥተ ሰማያትን ሊሰጣችሁ የሰማያዊ አባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ በማለት የሰው ወገናችን መንጋ በሚለው ቃል ገልጧቸዋል እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል» ከእነዚህ በጐች ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምጼንም ይሰማሉ አንድም መንጋ ይሆናሉ» በማለት ተናግሯል የዮሐ- ወን ፲-፲፮ ።

በሐዋርያት ሥራ ምዕ፡፳ ቁጥ-፳፰ ላይ ደግሞ «በገዛ ደሙ የዋጀትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ እኔ ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንደሚገቡባችሁ ደቀ መዛሙርቱንም ወደኋላቸው ይስቡ ዘንድ ከፉ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ» የሚል ተጽፎ እንመለከታለን ። እንዲሁም ሐዋርያው ጴጥሮስ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርንመንጋ ጠብቁ ለመንጋውም ምሳሌ ሁኑ ይላል ፩ኛ ጴጥ- ፭—፫ ።





ሰብአ ሰገል በቤተ ልሔም ለተወለደው ኢየሱስ ወርቅ ዕጣን ከርቤ ለመስጠት በግመሎቻቸው ላይ ይጓዛሉ ።

ይህ ሁሉ የሚያስረዳው በመንጋ የተመሰሉ ምዕመናን በጠባቂዎች ተመስለው የተነገሩት ደግሞ አስተማሪዎች መሆናቸውን ነው እንደዚህ ከሆነ አስተማሪዎች ምእመናንን የማስተማርና ከክህደትና ከኑፋቄ የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው።



በመንጋ የተመሰሉትም ምእመናን በመካከላቸው ስምምነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል መንጋዎች በመካከላቸው ስምምነት ከሌለ በአንድነት በመሰማራት ውሀ ተጐንጭተው ሣር ነጭተው ለመኖር እንደማይችሉ ምእመናንም በመካከላቸው ስምምነት ፍቅር ሰላምና አንድነት ከሌለ በኅብረት እግዚአብሔርን ለማመስገን አይችሉም ።

ማንኛውም ፍጡር በኅብረት ሆኖ ፈጣሪውን ማመስገን እንደሚገባው ነቢዩ ኢሳይያስ ምዕ. ፲፩ ፮—፱ ሲናገር ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል ጥጃና የአንበሳ ደቦል በአንድነት ያርፋሉ ታናሽም ልጅ ይመራቸዋል ላምና ድብም አብረው ይሠማራሉ ግልገሎቻቸውም በአንድነት ያርፋሉ አንበሳም እንደበሬ ሣር ይበላል የሚጠባውም ሕፃን በእባብ ጉድጓድ ላይ ይጫወታል ጡት የጣለውም ሕፃን በእፉኝት ቤት ላይ እጁን ይጭናል በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ፤አይጐዱም ፤ አያጠፉም ውሀ ባሕርን እንደሚከድን ምድርም እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና » ይላል ።

ነቢዩ ከዚህ በላይ እንደተናገረው እነዚህ ፍጥረታት ሁሉ በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ሰላምንና ፍቅርን አንድነትንም አግኝተው ተደስተዋል ይህንንም የሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሲገልጽ «ወኩሉ ፍጥረት ተፍሥሐ በምጽዓትከ » ወደ ዚህ ዓለም በመምጣትህ ፍጥረቱ ሁሉ ደስ አለው ብሏል በዕለተ ልደት ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በኅብረት ሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቀረቡት መላእክትና እረኞች ናቸው ጌታችን በቤተ ልሔም በላሞች በረት ሲወለድ የተገለጸው ለእነርሱ ስለሆነ በአንድነት ሆነው «ክብር ምስጋና ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ» ብለው ካመሰገኑ በኋላ መላእክት ወደሰማይ ሲወጡ እረኞች ወደየቤታቸው ሂደው ይህንን እግዚአብሔር የገለጸልንን ታላቅ ምሥጢር ልንደብቀው አይገባንም ብለው የልደቱን የምሥራች ለወገኖቻቸው አበሠሯቸው ሉቃስ ፪፡፲፩።

ይህንን መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ስለ ጌታችን ልደት በዘመረበት የአስተምሮ ድጓ ላይ «ዮም- አሐደ መርኤተ ኮኑ» ዛሬ መላእክትና ሰዎች አንድ መንጋ ሆኑ ክርስቶስን በሃይማኖት ቃል ያመሰግኑት ዘንድ» ብሏል እንዲሁም የተለያዩ ፍጥረታት የተለያዩ ገጸ በረከቶችን ለክርስቶስ ልደት ማቅረባቸውን ሲገልጽ «በአንተ ልደቱ ለክርስቶስ አድባር ኮኑ... ስለ ክርስቶስ መወለድ ተራሮች የሕይወት ኅብስትን ሆኑ የዱር እንጨቶችም የበረከት ፍሬን አፈሩ የባሕር ውሃም ወተትንና ማርን ሆነች መላእክትም ተሰብስበው በሕፃኑ እናት በድንግል ማርያም ላይ ክንፋቸውን ጋረዱ» ይላል እንዲሁም ሰብአ ሰገል ወርቅ ፤ ዕጣን ( ከርቤ ይዘው መጥተው ለኢየሱስ ካበረከቱ በኋላ እጅግ በጣም መደሰታቸውን ሲገልጽ » አንፈራጹ ሰብአ ሰገል አምኃኖሙ አምጽኡ መድምመ ረኪቦሙ ሕፃነ ዘተወልደ ለነ » ሰብአሰገል የተወለደውን ሕፃን (ኢየሱስን ) አግኝተው መባቸውን ከሰጡ በኋላ ዘለሉ ተደሰቱ ብሏል ። ይህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ዕለት ፍጥረቱ ሁሉ በጠቅላላ የተደሰተበት ዓቢይ በዓል በመሆኑ እንደቀላል ነገር ልንመለከተው አይገባም ይህንን ዓቢይ ልደት ከታናናሾች ፍጥረታት ጀምሮ እስከታላላቆች ድረስ በልዩ ልዩ ስጦታ እንዳከበሩት ተመልክተናል ።

የሌሎችን ፍጥረታት ስጦታዎች እየተመለከትን በአንክሮ ብቻ ማለፍ የለብንም የበዓለ ልደቱ ተካፋዮች ለመሆን የምንችልበትን ገጸ በረከት የማቅረብ ግዴታ አለብን አንዳንድ ሰዎች በዓለ ልደቱን በምን ዓይነት መንገድ ማክበር እንደሚገባ ባለመረዳታቸው የበዓሉ ዕለት ያለ መጠን በልተው ሲጨነቁ ይውላሉ፤ሌሎችደግሞ ከአቅማቸው በላይ አብዝተው ጠጥተው ሠክረው ሰውን ሲሰድቡ፤ሲያዋርዱ ወዘተ ይውላሉ እንዲሁም ከሥካር የተነሣ በየመንገዱ እየወደቁ የገዛ ሰውነታቸውን ከመጉዳት የሚደርሱም እንዳሉ እያጠራጥርም እንግዲህ ይህንንና ይህንን የመሳሰሉት ተግባሮች ሁሉ የበዓሉን ዓላማ የሚከተሉ ሳይሆኑ ከዓላማው ውጭ ስለሆኑ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ እንደነዚህ ካሉ አስነዋሪዎች ተግባሮች የመጠንቀቅና የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

በዓሉ መንፈሳዊ እንደመሆኑ መጠን መከበር ያለበት በምስጋና፤በጸሎት፤የተራቡትን ምግብ ይዞ በመጠየቅ ፤ ያዘኑትን በማጽናናትና መንፈሳውያን ሥራዎችን በመፈጸም ነው።

ሰብአ ሰገል ለተወለደው ሕፃን ኢየሱስ መባቸውን አቅርበው እንደዘለሉ ከላይ ተገልጿል እኛ በዚህ ዕለት መዝለልና መደሰት ያለብን ምስጋናችንና መባችንን ለክርስቶስ በማቅረብ ነው የምናቀርበውም ምስጋና በእኛው ብቻ መወሰን አይኖርበትም እረኞች ከመላእክት ጋር እንደ አንድ መንጋ በመሆን ክርስቶስን ካመሰገኑ በኋላ ይህንን ያየነውን ታላቅ ምሥጢር ለወገኖቻችንም መግለጽ አለብን በማለት ሂደው ለወገኖቻቸው እንደተናገሩ እኛም የልደቱን የምሥራች ላልሰሙት የማሰማት ግዴታ አለብን።

እኛን ለማዳን ሲል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ከድንግል ማርያም የተወለደውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት ጋር እንደ አንድ መንጋ በመሆን ዘወትር «ክብር ምስጋና ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ» እያልን እናመስግነው ስለልደቱም ተሳታፊዎች መሆናችንን ለመግለጽ የምንችለው በምስጋናና በልዩ ልዩ መንፈሳውያን ሥራዎች መሆኑን እንዘነጋ ።

ቄስ ልሳነወርቅ በዛብኅ



www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስ ሲኖዶስ ትርጉምና ዓላማው
## ሲኖዶስ ማለት ጉባኤ ማለት ነው

ስለቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ሐዋርያት ከጌታችን ዕርገትና መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ሳይበታተኑ በአንድነት በኢየሩሳሌም ሳሉ የወሰኑት ውሳኔ የሠሩት ሥርዓት ሲኖዶስ ይባላል ፤ ሲኖዶስም ጉባኤ ማለት ነው ፤ ይኸውም ጌታችን ባስተማረው በአራቱ ወንጌላት ልክ አራት ክፍል አለው ። እነዚህም ትእዛዝ ፤ ግዕው ፤ አብጥሊስ ፤ ሥርዓተ ጽዮን ይባላሉ ። መጽሐፎቹ ብዙ የቤተ ክርስቲያንን ጉባኤ ውሳኔ አጠቃለው የያዙ ናቸው ሐዋርያት በዚያን ጊዜ ሕዝቡን ለማስተማር ለስብከተ ወንጌል ይፋጠኑ ነበር ። ለጊዜው ለቢጸ ሐሳውያን መቃወሚያና በጊዜያቸው ለነበረው ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መመሪያ መንፈስ ቅዱስ እየረዳቸው ይህን በአንድነት በየጊዜው በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የሚወስኑትን ውሳኔዎች ወደፊት የሚነሡ ሊቃውንት ይወስኑ ብለው በየሀገረ ስብከታቸው ተበታተኑ ። ወንጌልንም ዞረው አስተማሩ ።

፫ኛውና ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመ አምልኮ ባዕድ የበዛበት ዘመን ከመሆኑም ሌላ በቤተ ክርስቲያን አንድነት መካከል ክህደትና ኑፋቄ ተፈጥረው ብዙዎች ሊቃውንት እርስበእርሳቸው ሲለያዩ ፫፻፲፰ ሊቃውንት የቀናውን ሃይማኖት ይዘው በማስተማር ተገኝተዋል ። በዚህ ጊዜ ሲኖዶስ አድርገው በጊዜው የተነሡትን ከሃድያን እነ አርዮስንና ሌሎችንም ከቤተ ክርስቲያን በሲኖዶሳቸው ማለት በጉባኤያቸው ለይተው ሃይማኖትን አጽንተው በየደረጃቸው ለሚገኙ ማለት ለቀሳውስት፤ ለመነኮሳት ፤ ጻድቃን ለነገሥት ለምእመናን ሃይማኖት የሚጸናበትን ምግባር ትሩፋት የሚቀናበትን በጠቅላላ ቤተ ክርስቲያን በውስጥና በአፍአ የምትስፋፋበትን ብዙ መጻሕፍትን ጽፈውልናል ። ይኸውም የሐዋርያት ሲኖዶስና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛ የሆነው የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ሲኖዶስና ልዩ ልዩ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ነው ። ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የኦሪትን ፤ የነቢያትን ፤ ትንቢትና ምሳሌ ተረድታ የክርስቶስን መምጣት በተስፋ ስትጠባበቅ የነበረች



ብፁዕ አቡነ ኤልሳ ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ።

ሀገር እንደመሆኗ መጠን ከመጀመሪያው መቶ ዓ- ም- ጀምሮ የጌታችን የመድኃኒታችን የ ኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ተቀብላለች ። ወደ ኢትዮጵያ ትምህርተ ወንጌልን ይዞ እንዲመጣ ፈቅዳ የላከችው የመጀመሪያው የወንጌል ሐዋርያ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ነው ። እርሱም የወንጌልን ትምህርትና ሥርዓት ይዞ በመጣ ጊዜ የሐዋርያትንና የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ሲኖዶስ ውሳኔ አብሮ መጥቶልናል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን በክብር ተቀብላዋለች ። የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ከሐዋርያት ለሊቃውንት ፤ ከሊቃውንት ለነሱ የተሰጠውን ኃላፊነትና አደራ ተቀብለው የሐዋርያትንና የሊቃውንትን የጸሎትና የሱባኤ ጊዜያቶች በማክበር ሲኖዶስ እያደረጉ ይገኛሉ ። ቤተ ክርስቲያናችን እስከአሁንም ሆነ ወደፊት የምትስፋፋባቸውና የምትጠብቃቸው ሊቃውንት መናፍቃንን የሚረቱበት ፤ መናፍቃን የሚደክሙበትና የሚያፍሩበት የሲኖዶስ ውሳኔና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በሊቃውንት እየተመረመሩ በቤተ ክርስቲያናችን መመሪያና ቅርስ ሁነው ይገኛሉ ።

ከዚህም ሌላ አንዳንድ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በመለወጥ ቤተ ክርስቲያናችን የሐዋርያትና የሊቃውንት ሥርዓት እንደሌላት ምዕመናንም ሥራቱን ከሊቃውንት እንዳልተረዱ በማድረግ የተሳሳተ ትምህርት ሲሰጡ ይታያሉ ።

እንግዲህ የቅዱስ ሲኖዶስ ዓላማ ይህንንም የመሳሰለውን ትምህርት መቃወም ነው ቤተ ክርስቲያንም ትቃወማለች ። በተጨማሪም የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ዓላማም ቤተ ክርስቲያናችን በሐዋርያትና በሊቃውንት እምነትና ሥርዓት ጸንታ ምእመናን እንዲበዙ መንፈሳውያን ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን የበለጠ አገልግሎትና ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፤ አብያተ ክርስቲያናት የቀደሙት እንዲታደሱ ፤ አዳዲስ እንዲሠሩ ፤ ሰበካ ጉባኤው ተጠናክሮ ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን ለይታ እንድታውቅ የራቁ እንዲቀርቡ ፤ ያላመኑት እንዲያምኑ ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ለምእመናን የሚዳረሱበት መንገድ እንዲፈለግ ታደርጋለች ።

በተለይ ካህናት ዲያቆናት ፤ መዘምራን ፤ በየደረጃቸው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አውቀው የጸናች ሃይማኖታቸውን በተርታ ነገር ሳይለውጡ ምእመናንን እንዲጠብቁ ፤ ከዚያም አስቀድሞ ጥንታውያን ሊቃውንት የሚገኙበት ት/ ቤት በችግር ምክንያት እንዳይፈታ ከዚህም ሌላ አምስቱ የካህናት ማሠልጠኛዎች ሥራቸውን እንዳያቋርጡና ካህናት እንዲማሩ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ዓላማው ነው ። ይህም ባለፉት ዓመታት ተተርጉሞ ታይቷል ።



# የመጀመሪያ ተጠሪ ሐዋርያ

ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል በመጀመሪያ የተጠራ የጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነው።እርሱም የቤተ ሳይዳ ተወላጅ ነበር ። እንድርያስ ከመጠራቱ በፊት ዓሣ አጥማጅ ነበር ። በዚህም ላይ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር እንደነበረ በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ተገልጦአል።

እንድርያስ በመጀመሪያ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዘንድ ፕሮቶክሌቶስ እየተባለ ይጠራ ነበር።ይህም ተጠሪ ማለት ነው ።

እንድርያስ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ፲፫ ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል ። ፲፪ ጊዜ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ሲሆን አንድ ጊዜ ብቻ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ነው ከዚህም ሌላ ከአሥራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት አንዱ በመባል የተጠቀሰው ሐዋርያ እንድርያስ እንደሆነ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ይተረጉማሉ /ማር ፲፫፥፫/።

እንድርያስ በሐዋርያት የስም ዝርዝር ውስጥ (ሊስት) በማርቆስና በሐዋርያት ሥራ አራተኛ ተራ ቁጥር ላይ ይገኛል ። በማቴዎስና በሉቃስ ደግሞ በሁለተኛ ተራ ቁጥር ላይ ተመዝግቦአል ።

ቅዱስ እንድርያስ ከማንኛውም ሰው ጋር የመግባባት ችሎታ የነበረው ሐዋርያ ስለነበረ ከሐዋርያት መካከል እንደ አስተባባሪ ሆኖ ይጠራል ። ለምሳሌ መጥምቁ ዮሐንስን ይከተል በነበረበት ጊዜ «እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ»የሚለውን ሀዋጅ ሲሰማ ዮሐንስን ትቶ ክርስቶስን ተከተለ። ክርስቶስ የት እንደሚያድርና እንደሚውል ተረዳ ። ወዲያውም ወደቤቱ ሄዶ «ክርስቶስን (መሲሕን) አግኝተናል» በማለት ለወንድሙ ለጴጥሮስ ነገረው ከክርስቶስም ጋር አስተዋወቀው ስለዚህም የቤተሰብ ሐዋርያ ተባለ።ምክንያቱም ራሱ በቅድሚያ ክርስቶስን ካገኘና ካመነ በኋላ ክርስቶስን የሰበከ በቤቱ ውስጥ ለወንድሙ ነውና ።

ከዚህም ጋር እንድርያስ የወጣቶች ሐዋርርያ ይባላል ። መድኃኒታችን ክርስቶስ ይከተሉት የነበሩት ሰዎች ተርበው ባያቸው ጊዜ የሚበላ አንዳች ነገር አላችሁን» ሲል ቢጠይቅ ፊልጶስ ምንም እንደሌላቸው መለሰለት እንድርያስ ግን«አምስት እንጀራና ፪ ዓሣዎች የያዘ ወጣት ከዚህ አለ» በማለት ለክርስቶስ ተናገረ።ቀጥሎም ወጣቱን ወደ ክርስቶስ አቀረበው ። ጌታም የወጣቱን እንጀራና ዓሣ አበርክቶ ለአምስት ሺህ ሰዎች መገበ። በዚህም ምክንያት እንድርያስ የወጣቶች ሐዋርያ ለመባል ችሎአል ።

ይህ ብቻ አይደለም እንድርያስ የአሕዛብ ወዳጅ አይሁዳዊ እየተባለ ይጠራል ። መድኃኒታችን ክርስቶስ በፋሲካ በዓል ላይ በኢየሩሳሌም ተገኝቶ ሳለ በዚያ ጊዜ በአይሁድ ኅብረተሰብ ዘንድ አሕዛብ እየተባሉ የሚጠሩት የግሪክ ሰዎች በዓሉን ለማየት ተገኝተው ነበር ። እነርሱም ጌታችን ኢየሱስን ለማየት ፈልገው የሚያገናኛቸው ሲፈልጉ ፊልጶስን አገኙና «ጌታ ክርስቶስን ልናይ እንወዳለን» አሉት ፤ ፊልጶስም ወደ እንድርያስ አቅርቦ አስተዋወቃቸው ።

ሐዋርያው እንድርያስ አይሁዳዊ ሲሆን እንደ አይሁድ አሕዛብን ሳይጸየፍ ክርስቶስን እንዲያውቁ በማድረጉ የአሕዛብ ሐዋርያ የአሕዛብ ወዳጅ በመባል ዝነኛነትን አግኝቶአል።እንድርያስ ስለ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ምልክት ከጠየቁት ደቀመዛሙርት አንዱ ነው። ይህም እንግዳ ነገርን ለማወቅ የመጠየቅ ጠባይ እንደነበረው ያሳያል ።

እስካሁን በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ቅዱስ እንድርያስ የተጻፈውን ተመልክተናል ። ቀጥሎም በትውፊት ስለ እንድርያስ የተመዘገበውን እናያለን። ትውፊት እንደሚነግረን እንድርያስ የግሪክና የሩሲያ የእስኮትላንድ ጠባቂና ተራዳኢ ቅዱስ ነው። ይባላል ። አውሳብዮስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ፫ም- ፩ቁ- እንደጻፈው እንድርያስ እስኩቴስ በተባለ አገር ወንጌልን አስተምሮአል ። እስኩቴስ በጥንቱ ዓለም አጠራር በርባሮስ የሚባለው ነው። ይህም አገር የሚገኘው ከጥቁር ባሕር በስተሰሜን ዳንዩብና ታናይስ በተባሉ ወንዞች መካከል ነው ። ዛሬ ግን በዘመናዊው ዓለም አጠራር በጠቅላላ ሩስያ ተብሎአል። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የእስኩቴስ ሰዎች በዚያ ዘመን ከአራዊት ያልተሻሉ ጨካኞች እንደ ነበሩ ይናገራል/ ዮሴፍ አጊንስት አጲያን ፪፻፷፬/። ቅዱስ እንድርያስ በእነዚያ ብሔረ ሰቦች መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን በመስበኩ የሩሲያ ተራዳኢ ቅዱስ እንደተባለ በትውፊት ይነገራል ።

በተጨማሪም ቅዱስ እንድርያስ በቢታንያ ፤ በገላትያና በቢዛንታይን /ቁስጥንጥንያ/ ወንጌልን አስተምሮአል እነዚህም አገሮች በግሪክ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በሩማንያም ወንጌልን እንደሰበከ የሩማንያ ቤተ ክርስቲያን ትመሰክራለች።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ የተቸነከሩ እጆቹን ለእንድርያስ እንዳሳየው በትውፊት ይነገራል ።ቅዱስ ያሬድ ይህን ሲገልጥ ለእንድርያስም የእጆቹን ችንካሮች አሳየው ብሎአል።ይህም ቅ/እንድርያስ ለክርስቶስ ትንሣኤ እውነተኛ ምስክር እንደሆነ ያመለክታል ።

በመጨረሻም ቅ/እንድርያስ በግሪክ ውስጥ በአካይያ አውራጃ ጳጥራስ በተ

ተከታዩ ወደ፲፫ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አካባቢ የሚከናወኑት የልማት ተግባሮች አንድ ዓይነት አይደሉም የትምህርት ፤ የተግባረ ዕድ ፤ የእርሻ ፤ የቁፋር ፤ የከብት ዕርቢ የመሳሰሉትም ይከናወናሉ ።


ከሚከናወኑትም የልማት ሥራዎች አልፎን አልፎን በመጽሔታችን ላይ የምናሠፍራቸው በንቃትና በትጋት የሚሠሩትን ለማበረታታት ሲሆን ፤ የልማት ተግባር ሳይጀምሩ የተቀመጡትን እንዲጀምሩና እንዲሠሩ ለማነቃቃት ነው ።

በአሁኑ ጊዜ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የልማት ተግባር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘባቸው አቅም ያላቸው ለብቻቸው አቅም ያነሣቸው ደግሞ በመተባበር የልማት ተግባሮችን ለማቋቋም በመጣር ላይ ይገኛሉ ። ይህም በተሐድሶ ጉዳና ለምትገኘው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ አስተዋፅኦን የሚያበረክት ነው ።

ባለፈው እትማችን ስለጉፋ ቅዱስ ገብርኤል ዕደ ጥበብ ማሠልጠኛ ት/ቤት መግለጻችን ይታወሳል ። በዛሬው እትማችን ደግሞ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አካባቢ ስለሚካሄዱት የልማት ሥራዎች እንመለከታለን ። ቀደም ሲል ቢመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በርከት ያሉ የልማት ተግባሮች መቋቋማቸው የሚታወስ ነው ። አሁን በጽሑፋችን ለመግለጽ የምንፈልገው ተቋቁመው ነበር ስለሚባሉት ሁሉ ሳይሆን ፤ አሁን በሥራ ስለሚገኙት የልብስ ተክህኖ ስፌትና የሙካሽ ሥራ ነው ።

እነዚህን ሁለት የሥራ ክፍሎች በበላይ ሆነው የሚመሯቸው አቶ ምትኩ ለማ ናቸው ። አቶ ምትኩ የሚሰፉትን ልብሰ ተክህኖች ሁሉ እየመጠኑ እየለኩ በመቅደድ ለሠራተኞች ከማቅረባቸውም ሌላ ራሳቸውም ይሰፋሉ ። በልብሰ ተክህኖው ስፌት የተመደቡት ሠራተኞች ቁጥር ከእርሳቸው ጋር ሰባት ናቸው ። ሰባቱም ሠራተኞች በሥራ ጊዜ ከሥራው ቦታ ለአንዳፍታ እንኳን እንደማይለዩ ጠይቀን ተረድተናል ። ነገር ግን ለእያንዳንዳቸው የስፌት መኪና አልተዘጋጀላቸውም ። ከላይ እንደ ተጠቀሰው የሠራተኞች ቁጥር ሰባት ሲሆን ፤ የሚሰፉባቸው መኪናዎች ሁለት ብቻ ናቸው ። ሠራተኞቹም እየተጠባበቁ በፈረቃ ይሠራሉ እንጂ ሌላ የተለየ ተግባር የላቸውም አቶ ምትኩን ስለሥራው አንዳንድ ጥያቄዎችን አቅርበንላቸው መልስ ሰጥተውናል ።

ይህ የልብሰ ተክህኖ ስፌት በስንት ዓመተ ምሕረት እንደተጀመረና ሲጀመር ስንት ሰዎች እንደነበሩ ቢያስረዱን ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች ሲመልሱ ፤ የልብሰ ተክህኖው ስፌት ሲጀመር እኔ አልነበርኩም ። ነገር ግን ጠይቄ እንደተረዳሁት ከሆነ አሁን ከአሥራ ስምንት ዓመታት በላይ ሆኖታል ፤ ሠራተኞች ግን ብዙ አልነበሩም ። በአንድ ሰው ብቻ ነው የተጀመረው እኔ ከዚህ ቦታ መጥቼ ሥራውን የጀመርኩት በ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. ሲሆን በዚያን ጊዜ ሌላ ረዳት ሰው አልነበረኝም ። የምሰፋው እኔ ብቻየን ነበር። ከጊዜ በኋላ ግን ሠራተኞች ጥቂት በጥቂት እየተጨመሩ አሁን ከሰባት ደርሰናል ብለዋል ።



የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ልብሰ ተክህኖ ሰፊዎች በሥራ ላይ እንዳሉ ይታያሉ ።

**ጥያቄ ፤** በአንድ ወር ውስጥ ለስንት አብያተ ክርስቲያናት ልውካን ለመስፋት ትችላላችሁ ? ፤

**መልስ ፤** የሚያስፈልገው ሱቲ ( ልብስ ) ከቀረበልን በአንድ ወር ውስጥ ለሃያ አብያተ ክርስቲያናት ልውካን ልብሶችን ሰፍተን ለገቢያ ለማቅረብ እንችላለን ። ይህንንም ስል ለአንድ ቤተ ክርስቲያን የአምስት ልውካን ልብሶችን ማለቴ ነው ።

**ጥያቄ ፤** ለልብስ የሚሆኑትን ሱቲዎች እንደፈለጋችሁ ለማግኘት ትችላላችሁ ? ወይስ ችግር አለባችሁ ?

**መልስ ፤** ሱቲዎቹ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ስለሆኑ ብዙም ችግር የለብንም ፤ ካቴድራሉ በወቅቱ እየገዛ ያቀርብልናል ።

**ጥያቄ ፤** ካቴድራሉ ፤ ሊያቃልልላችሁ የሚችል ችግር ከአለባችሁ ብትገልጹልን ?

**መልስ ፤** በሥራችን ላይ አንዳንድ ችግሮች መኖራቸው የሚያጠያይቅ አይደለም ሁሉንም ችግር ለመግለጽ ባያስፈልግም ፤ አንዳንዶቹን መግለጹ ተገቢ ይመስለኛል ።

ሠራተኞቹ በቁጥር ሰባት ስንሆን የምንሰፋባቸው መኪናዎች ሁለት ብቻ ናቸው ስለዚህ አራታችን ስንሰፋ ሦስቱ መቀመጥ ይኖርባቸዋል ይህንን ከቴድራሉ ለማቃለል የሚችል ይመስለኛል ሊያቃልለውም የሚችለው መኪናዎችን ገዝቶ አቅርቦ እንድንሠራ በማድረግ ነው ።

**ጥያቄ ፤** ልብሱን ከሰፋችሁ በኋላ በገቢያ ላይ የማዋል ችግር ይገጥማችኋል? ወይስ እንደተሰፉ ወዲያውኑ ይሸጡላችኋል ?

**መልስ ፤** ልብሶቹ ከተሰፉ የመሸጥ ችግሩ ይህንን ያህል የጐላ አይደለም የካቴድራሉ ሁለት ሱቆች ስላሉት ወደ እነዚያ ሱቆች እየተላኩ ይሸጣሉ ።

**ጥያቄ ፤** በዚህ የሥራ ክፍል ተመድበው የሚሠሩት ሠራተኞች የሥራ ውጤት እንኳን ትርፍ ሊያስገኝ የራሳቸውን ደመወዝ እንኳን አይችልም ይባላል ። ይህ ምን ያህል እውነት ነው?

**መልስ ፤** ከላይ እንደገለጽኩት ችግሩ የልብስ መስፊያ እጥረት ነው እንጂ መኪና ለእያንዳንዳችን ተሰጥቶን ብንሰፋ እንኳን ለእኛ ደመወዝ በእጥፍ ለማምረት እንችል ነበር ችግሩ የመኪና መስፊያ አለማግኘታችን ነው ።

**ጥያቄ፤** አሁን ከምትሠሩት ሥራ ሌላ በተጨማሪ ለመሥራት ያቀዳችሁት ሥራ እንዳለ ቢገልጡልን ?

**መልስ ፤** ወደፊት ለጃንጥላ የሚሆኑና በዋናው ቤተ ክህነት እየተሰፉ እንደሚሸጡት ያለ የልብስ ዓይነቶች ቢቀርቡልንና የልብስ መስፊያዎች መኪናዎችም በልካችን ቢሰጡን በርከት ያሉ የሥራ ውጤቶችን ለማቅረብ ዕቅድ አለን በማለት አቶ ምትኩ ለማ ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል በሙኳሽ ክፍል የሚሠሩትንም አነጋግረናቸው ነበር እነርሱ እንደሚሉት ለሙኳሽ ሥራ የሚሆኑት ጥሬ ዕቃዎች የሚመጡት ከውጭ ሀገር ስለነበር አሁን የዕቃዎች ዕጥረት ገጥሞናል አንዳንድ የሚያሠሩ ሰዎች ጥሬ ዕቃውን ካላስመጡልን ቦዝነን ነው የምንውለው ብለዋል ።

ለሙካሽ ሥራ የሚሆኑትን ጥሬ ዕቃዎች ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጠይቆ ለማስመጣት ይችል እንደሆነ ለምን አይጠየቅም ? በማለት ጥያቄ ለመንበረ ፀባዖት ቅ- ሥላሴ ካቴድራል ዋና ጸሐፊ ዲያቆን ከፍ ያለው መራሂ አቅርበንላቸው ሲመልሱ እስከአሁን ድረስ ይህንን ጥያቄ ለጠ/ቤተ ክህነት አላቀረብንም ። ወደፊት ግን ለማቅረብ እንሞክራለን ብለዋል። ጉዳዩ የአንድ ካቴድራል ብቻ ሳይሆን ፤ መላው አብያተ ክርስቲያናትን የሚመለከት ነው ። በሙካሽ ክፍል ተሠልፈው የሚሠሩት ሠራተኞች የ፲፰ ዓመታት ልምድ ያላቸው እጅግ በጣም የሠለጠኑ ናቸው ። ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሠራተኞች እንደ ቀላል ነገር ሳትመለከት ልትጠቀምባቸው ይገባል ።

ሠራተኞቹ የውጭ ሀገር ዕቃ እጥረት ገጠመ ተብለው ከሥራ እንዲቦዝኑ አያስፈልግም ። በሀገራችን አድባራትና ገዳማት ውስጥ የሚገኙት ልዩ ልዩ የሆኑ አልባሳት የወርቅና የብር ዝምዝማቸውና ጥልፋቸውእየ ተላቀቀ ሲወድቅ የሚያስጠግናቸው ( የሚያሠራቸው ) በማጣቱ ከፍተኛ ጉድለት ደርሶባቸዋል ። እየደረሰባቸውም ነው ። ታዲያ እንደዚህ ያለ ከፍተኛ ችግር እያለ እንደነዚህ ያሉትን የሠለጠኑትን ሠራተኞች መድቦ አለማሠራት እጅግ በጣም ሞኝነት ነው ። አባቶች « በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ቁጥር ነው » እንደሚሉት እነዚህን ሠራተኞች እንደዋዛ መመልከት ለቤተ ክርስቲያን አለማሰብ ነው ።

በዚህ ጉዳይ አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት ተመካክረው በየሀገረ ስብከታቸው ሠራተኞችን በመውሰድ ወይም



የካቴድራሉ ዋና ጸሐፊ ዲ. ከፍ ያለው መራሂ ፤

ዕቃዎችን ወደጠቅላይ ቤተ ክህነት በመላክ እንዲታደሱ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው ።

የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከአቋቋማቸው የልማት ዘርፎች ሁለቱን ጠቅሰናል ። በሁለቱም ላይ ያለውን ችግር በመጠኑ ጠቁመናል ። ካቴድራሉ በቅርቡ ጊዜ ሳይሰጥ ሊያሟላቸው ከሚችለው መካከል አንደኛ ለልብስ ሰፊዎቹ በልካቸው መኪናዎችን ገዝቶ ማቅረብ፤ ሁለተኛ ለጃንጥላና ለልብስ የሚሆኑትን ልብሶች እየመረጡ ማቅረብ ነው ። እንደዚህ የሆነ እንደሆነ የልማቱ ተግባር እየተጠናከረ የሥራው ውጤት እየበረከተና እያማረ ይሄዳል ። የስፌት መኪና ሳያቀርቡ ሠራተኞችን በፈረቃ እንዲሠሩ መመደብ ግን ለአንድ በሬ ዘጠኝ ገበሬ እንደሚለው የአባቶች ምሳሌ ይሆናል ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብኅ





www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

አንድ መንግሥት መልካም አመራር ያለውና የሕዝቡም አንድነትና ኅብረት የጠነከረ ሲሆን በአገሩ ውስጥ ሰላምና ብልጽግና እንደሚሰፍን ሁሉ በሁለት ጾታዎች ማለት በባልና ሚስት መካከል በፈቃደ እግዚአብሔር በተፈጸመው ጋብቻ ውስጥ የሚመሠረተው ቤተሰብም ንጹሕ ፍቅር ፤ መተሳሰብና ሰላም የሰፈነበትና አንድነቱ እስከ መጨረሻው የጸና ይሆናል ። በዚህ ምክንያት ሁለት የነበሩት ሰዎች ከጋብቻ በኋላ አንድ ሥጋ ተብለው ይጠራሉ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ድንቅ ምሥጢር» ተብሎ ይታወቃል ።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ጋብቻ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንዱ ተቆጥሯል ። ምክንያቱም በውስጡ ሁለት ድንቅ ምሥጢርን ያዘለ በመሆኑ ነው፤ይኸውም የሚታይ አገልግሎት፤የማይታይ ጸጋ ተብሎ ይታወቃል ሁለት ወጣቶች ተዋህደው ተስማምተውና በፍቅር ተሳስረው ጋብቻን ሲፈጽሙ ይታያሉ ። ነገር ግን አንድ ሥጋ ሆነው ሲዋሃዱ አይታዩም አንድ መሆናቸው የሚገለጸው ሁለቱ በሚያፈሩት ፍሬ ነው የሚወለደው ልጅ ያንቺ ያንተ የኔ ነው ለማለት አይቻልም የእኛ እንጂ ።

ስለዚህ«ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» በሚል ቃል ወንጌላዊው ማቴዎስ አጠቃሎታል ።

ስለሆነም እግዚአብሔር በፈቃዱ ለሰዎች ላዘጋጀው ልዩ ድንቅ ምሥጢር ሰዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉለት ይገባል ፤ በተለይም ክርስቲያኖች መልካም ጋብቻን ለመመሥረት የሚከተሉትን ማወቅና መጠበቅ ይኖርባቸዋል ።

፩ኛ/ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ መጽናት ፤ ሁለቱም ጾታዎች በአንድነት ተሳስረው ቤተሰብ ከመሠረቱ በኋላ ወደሌላ ቢሄዱ ፊት የነበሯቸው ንጹሕ ፍቅርና መተሳሰብ ስለሚቀነሱ እርስ በእርሳቸው መለያየት ይሆናል ። ይህም እግዚአብሔር ያከበረውን ሕግ ማፍረስ ስለሆነ በነፍስም በሥጋም ከማስወቀሱና ከማስቀጣቱም ሌላ የቤተሰብን ክብር ያሳጣል ።

፪ኛ/መልካም ቤተሰብ በንጹሕ ፍቅርና በሁለቱ ጾታዎች መካከል ባለው መልካም መግባባት መመሥረት አለበት ፍቅር የሌለው ጋብቻ ጨው የሌለው ወጥ ስለሆነ ጣዕም የለውም ። በፍቅር የተመሠረተ ቤተሰብ ግን ምንም ዓይነት ችግር የማይፈታው በመሆኑ ዘለዓለማዊ ነው ፍሬውም እስከመጨረሻው ያማረ ይሆናል ።

፫ኛ/ ጋብቻ ከሥጋ ዝምድና የራቀ መሆን አለበት አንድ ክርስቲያን በምንም ዓይነት የእኅቱን ወይም የወንድሙን ልጅ ማግባት በሕገ ቤተክርስቲያን የተከለከለ ነው ። ምክንያቱም በንጹሕ ፍቅር በመተሳሰር በጋብቻ ምክንያት የሚፈጠረው ዝምድና የላቀና የከበረ በመሆኑ አባቶቻችን እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ሰዎች እንዲጠባበቁ ሥርዓት ሰርተዋል እኛም ልጆቻቸው ይህንን ጠብቀን ማቆየት ግዴታችን ነው ።



የ፶ኛ ዓመት ጋብቻቸውን በቅዱስ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን ሐምሌ ፳ ቀን ፹፩ ዓ ም ያከበሩት አቶ ሁንዴ ሚሌና ባለቤታቸው ወይዘሮ ሙሉነሽ ገመዳ ከቤተ ሰቦቻቸው ጋር ፤



፬ኛ/ ማንኛውም ከፍተኛ ነገር በምስክር ፊት ቢደረግ የጸና እንደመሆኑ መጠን በሕገ ቤተክርስቲያንና በእግዚአብሔር ቅዱስ መንበር ፊት የተደረገ ጋብቻም ፍጹም የጸና ይሆናል ። በዚህ ሁኔታ ጋብቻቸውን ፈጽመው የቆዩ ቤተሰቦች ምሳሌነታቸው በዚህ ጊዜ ቢጠቀስ ውጤቱ የላቀ ይሆናል ። ስለዚህም በትንሣኤ መጽሔት እየተዘጋጀ በሚቀርበው «የቤተሰብ ዓምድ» እንደነዚህ ዓይነት ቤተሰቦችን ስናስተዋውቃችሁ ቆይተናል በዚህ ዓምዳችንም የምናስተዋውቃችሁ ቤተሰብ የመሠረቱት ጋብቻ የዕድሜ ልክ መሆኑን በመገንዘብ የሃምሳ ዓመት የጋብቻ በዓላቸውን ያከበሩትን ነው ።

እነርሱም አቶ ሁንዴ ሚሌና እመት ሙሉነሽ ገመዳ ከነቤተሰቦቻቸው ናቸው ። እነዚህንም አዛውንቶች ለማስተዋወቅ ዓቢይ ምክንያት የሆነን ከላይ እንደተገለጸው ለመጪው ትውልድ የሚሆን ትምህርት ከእነዚህ ዓይነት ቤተሰቦች የሚገኝ መሆኑን በማመን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ «የሃምሳ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዩ የጋብቻ በዓላቸውን» ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ-ም ያከበሩበትን ዕለት ምክንያት በማድረግ በዚህ የጋብቻ ዘመናቸው ውስጥ ስለአሳለፉአቸው አንዳንድ ሁኔታዎች በመጠየቅ ያገኘነው ትምህርት የሚሰጥ ስለሆነ ቀጥሎ አቅርበነዋል። አቶ ሁንዴ ሚሌና የ፹፫ ዓመት ዕድሜ ያላቸው አዛውንት ሲሆኑ ባለቤታቸውን እመት ሙሉነሽን የሚበልጡአቸው በ፮ ዓመት የዕድሜ ልዩነት ብቻ ነው ።

እነዚህ ሁለት አዛውንቶች ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን በደረሱ ጊዜ እንደ ሀገሩ ባህልና ወግ መሠረት ቤተሰቦቻቸው ዳሩአቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አብረው በመኖር ያሳለፉትን «የሃምሳ ዓመት» የጋብቻ በዓላቸውን ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ-ም ለማክበር በቅተዋል ። በዚህ ጊዜ ቤተሰቦቻቸውና ልጆቻቸው እንዲሁም የልጅ ልጆቻቸውና ዘመድ ወዳጆቻቸው በተገኙበት በቅ/ዑራኤል ቤተክርስቲያን በታላቅ ሥነ ሥርዓት አክብረው ውለዋል።

በዚህ የሃምሳ ዓመት የጋብቻ ዘመናቸው ውስጥ ስለአጋጠሙአቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ሲያወሱ መልካሙንም ሆነ ክፉውን ጊዜ አብረን አሳልፈናዋልሁሉንም እንደየአመጣጡ መልሰነዋል፤ይላሉ በተጨማሪም አቶ ሁንዴ ሲናገሩ ከዚህ ውስጥ ያዘንበት ጊዜ ቢኖር አብረን ሆነን ችግር ለምን አየን በሚለው አልነበረም በዚሁ የጋብቻ ዘመናችን ፋሽስት ጣላት ወደ አገራችን ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ እኔም ለመዋጋት ከባለቤቴ ጋር አብረን ዘመትን በዚያም እያለን ለጥቂት ጊዜ ተጠፋፍተን ነበር በዚህ የተሰማን ኀዘን ለሁለታችንም እጅግ ጥልቅና መራራም ነበር ይህንን አንድ በሕይወቴ የደረሰብኝ ታላቅ ኀዘን አድርጌ እቆጥረዋለሁ ከዚያም በኋላ ስንገናኝ አብረን ፍሥሐ ያደረግንበት ዕለት ነው ይህን ከኀዘናችን አንጻር ስናየው ታላቅ ደስታን አስገኝቶልናል በመለያየታችን የደረሰብን ኀዘን ጣልያን ካጠፋውና ካወደመው ንብረታችን በላይ ነበር በተገናኘንበት ጊዜ ግን ለደስታዬ በእኔ በኩል ወደርም አላገኘለት በሷም በኩል እንዲሁ ነበር የሚታሰበው ከዚያ በኋላ የነበረን ሁሉ ጠፍቶ ስናገኘው አብረን በመሆናችን እየተጽናናን ኑሮን እንደገና መመሥረት ጀመርን ከዚያም በኋላ ስምንት ልጆች ወለድን ከነዚህም ውስጥ ሦስቱ ሲባረኩልን እነሱን እያየን እኛም የዕድሜ ባለጸጎች ሆነን በመገኘታችን ለነበረን ደስታ ተጨማሪ ደስታን አስገኝቶልናል ። አሁንም በተጨማሪ ደስታን ያስገኘልን ዛሬም ሳንለያይ ከዚህ ጊዜ ደርሰን ከልጆቻችንና ከልጅ ልጆቻችን መካከል ተገኝተን ፶ኛው የጋብቻ በዓላችንን ለማክበር በመብቃታችን ደስታን እንደገና ፈጥሮልናል ። እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባውና ከዚህም በኋላ በሚሰጠን ዕድሜ እሱን እያመሰገንን ለልጆቻችንም ዕድሜ አብዝቶ ሁሉንም ለማየት እኛ ከደረስንበት ዕድሜ ለመድረስ እንዲያበቃቸው መጸለይና መመኘት የዘወትር ተግባራችን ነው ሲሉ ሃሳባቸውን አጠቃልለዋል።

## የመጀመሪያ ተጠሪ . . .

ከ፬ኛው ገጽ የዞረ

ባለችው ከተማ በሰማዕትነት ዐርፎአል ሞቱም በመስቀል ነው ። ይሁን እንጂ ሰዎች ሊሰቅሉት በመጡ ጊዜ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት መስቀል አትስቀሉኝ ብሎ ስለጠየቃቸው በኤክስ ፊደል ዓይነት መስቀል ሰቅለውታል ይህም አይነት መስቀል እስካሁን ድረስ የቅዱስ እንድርያስ መስቀል በመባል ይታወቃል ። እንድርያስ በግሪክ በማስተማሩና በዚሁም በሰማዕትነት በመሞቱ የግሪክ ጠባቂ ቅዱስ ተብሎአል ።

በ፫፻፶፯ ዓ-ም ቄሳር ቆስጠንጢኖስ የእንድርያስን ዓፅም ከጳጥራስ ወደ ቢዛንታይን አስወስዶታል።በ፰ኛው ምእት ዓመት ደግሞ ሬጉሉስየተባለ መነኩሴ ከእንድርያስ ዓፅም የቀኝ እጁን ጣቶች ወደ እስኮትላንድ ወስዶአል ። ስለዚህም እንድርያስ የእስኮትላንድ ጠባቂ ቅዱስ ከመባሉም ሌላ በእስኮትላንድ የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን በእንድርያስ የተሰየመ ሲሆን የመጀመሪያውም ጳጳስ ሬጉሎስ ነው ።

ይሁን እንጂ የቅዱስ እንድርያስ ተራዳኢነቱና ጠባቂነቱ በግሪክ በሩስያና በእስኮትላንድ አይወሰንም ። በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ተራዳኢና ጠባቂ ቅዱስ ነው።በአጠቃላይ አነጋገር ዓለም አቀፍ ቅዱስ ሐዋርያ ነው። ስለዚህም በዓለም ያለችው ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በዓመት አንድ ጊዜ በዓሉን ታከብራለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ታሕሣሥ ፬ ቀን በታላቅ ሥነ ሥርዐት ታከብረዋለች ።

ሐዋርያው እንድርያስ ቤተሰቡን ይልቁንም ወንድሙ ጴጥሮስን ወጣቱንና የተናቁትን አሕዛብ ወደ ክርስቶስ እንደአቀረባቸው ከክርስቶስም ጋር እንደአስተዋወቃቸው ዛሬም «ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን» የሚሉት ሁሉ ወደ ጌታ መቅረብ እንዲችሉ በአማላጅነቱ ይለምናል ። ከአምላኩ ቃል ኪዳን የተሰጠው ቅዱስ ሐዋርያ ነውና።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የተባረከ ልደት

ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ከአባታቸው ከጸጋ ዘአብና ከእናታቸው ከእግዚእ ኃረያ ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፩፻፺፯ ዓ. ም. ተወለዱ ። እኚህ ጻድቅ አባት በኢትዮጵያ ምእመናን ዘንድ እጅግ የታወቁና ተወዳጅነት ያላቸው የ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገሥፅ የተባሉ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው ። ልደታቸውንም « የተባረከ ልደት» የሚያሰኘውም በዘመናቸው የፈጸሙት ታላቅ የወንጌል ሥራ ነው ።

በሥነ - መንግሥት የሚነገርላቸውና በዜና ገድል የሚተረከላቸውን ለባለታሪኩና ለባለ ገድሉ ትተን ሊካድ የማይቻለውን በዘመናቸው ያከናወኑትን የሐዋርያነት ሥራ በአጭሩ እንመለከታለን ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱበት አካባቢ ለተልእኮው የሚያስፈልጋቸውን ዕውቀት ከቀሰሙና መንፈሳዊ ትጥቅን በሚገባ ካደራጁ በኋላ በሃያ አምስት ዓመታቸው በማስተማር ሥራ ላይ ተሰማሩ ። ከዘመናቸው አስቀድሞ የክርስትና ትምህርት በሚገባ የተሰበከው በሰሜን ኢትዮጵያ ብቻ እንደነበር ከታሪክ እንረዳለን ። ስለሆነም አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ስብከተ — ወንጌል ያልደረሰው መሆኑ ግልጥ ነው ። በመሆኑም አቡነ ተክለሃይማኖት በዚህ ወቅት ለስብከተ —ወንጌል ሲሰማሩ በሥራው ላይ የገጠማቸው መከራና ተጋድሎ ከባድ መሆኑን መገመት አያዳግትም ። ቢሆንም በትእግሥትና በጸሎት ኃይል በእግዚአብሔር ቸርነት ችግሩን ተቋቁመውታል ።

ከዛሬ ፰፻ ዓመታት በፊት የነበሩት እኚህ ጻድቅ ሐዋርያ ከመሐል ሀገር ተነሥተው በማስተማሩ ተግባር በመሰማራት አብዛኛውን ኢትዮጵያ አዳርሰዋል ። ከሰሜን እስከ ደቡብ ፤ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከወሎ እስከ ወላይታ ፤ ከአሰቦት እስከ አሰላ በመጓዝ የወንጌል ብርሃን በአራቱ ማዕዘን ኢትዮጵያ እንዲያበራና እንዲስፋፋ አድርገዋል።ይኸውም ኢአማንያንን አስተምሮ በማጥመቅ ፤ የተጠመቁት በሃይማኖት እንዲጸኑ በቤተ ክርስቲያን በማደራጀትና አብያተ-ክርስቲያናትን በማሳነጽ ከፍተኛ ተልእኮ ፈጽመዋል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ማስተማርና ማጥመቅ ብቻ ሳይሆን ስለፍትሕ መጓደልና ስለአስተዳደር መዛባት ባለሥልጣኖችንና ነገሥታትን የሚወቅሱና የሚገስጹ ሐዋርያ ነበሩ። ይህም ባለ ሥልጣኖችን ስለከፉ ሥራቸው የመገሰፅ ጠባያቸው የመጥምቁ ዮሐንስን ይመስላል።ለዚህም አቶ ብርሃኑ ድንቄ«የኢትዮጵያ አጭር ታሪክ» በተሰኘው መጽሐፋቸው በገጽ ፵፪—፵፫ በዘመኑ የነበሩት መገሥፅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት . . . » በማለት ጠቅሰዋቸዋል ።

በዚህ አኳኋን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለ፳ ዓመታት ያህል የኢትዮጵያን ሕዝብ በማስተማርና በመምከር የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ ፈጽመዋል ። በዚህ የሐዋርያነት ዘመናቸው የወንጌል ሥራ ከዳር እስከዳር እንዲፈነጥቅ በማድረግ የተቀደሰ አገልግሎት አበርክተዋል ።

ጻድቁ ተክለሃይማኖት አብዛኛ ዕድሜያቸውን በሐዋርያነት ካሳለፉ በኋላ ቀሪውን የአረጋዊነት ዘመናቸውን በአንድ በአት ተወስነው ለመቆየት ስላሰቡ ፤ ለዚህ ተስማሚ የሆነ ቦታ መረጡ ። የመረጡትም ቦታ በሸዋ ክፍለ—ሀገር በሰላሌ አውራጃ የሚገኝ ምድረ ግራርያ ዛሬ «ደብረ—ሊባኖስ» በመባል የታወቀው ቦታ ነው ። በዚህም ቦታ ወንጌልን ካስተማሩ በኋላ ብዙ ደቀ—መዛሙርት አፍርተዋል ። ከደቀ መዛሙርቱም ፲፪ ንቡራነ—ዕድ መርጠው በመሾም ኢትዮጵያን በ፲፪ ሀገረ ስብከት ከፍለው ሰጥተዋቸዋል ። እነዚህ ፲፪ቱ ንቡራነ ዕድ በየሀገረ ስብከታቸው ተሰማርተው የአቡነ ተክለሃይማኖትን ስብከት በማጽናትና በማስፋት ፤ እርሳቸው ባልደረሱበትም ሁሉ በመጓዝ ኢትዮጵያን በወንጌል ትምህርት ያጥለቀለቁ ደቀ መዛሙርት ናቸው ።

ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያዊው ሐዋርያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ደብረ ሊባኖስ ሸለቆ በላይኛው ክፍል «ደብረ አስቦ» እየተባለ ከሚጠራው ዋሻ ሱባኤ ገብተው ተቀመጡ ይባላል ። በዚያም እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ቀሪውን ዕድሜያቸውን በጾም ፤ በጸሎትና በስግደት አሳልፈዋል ።

አቡነ ተክለሃይማኖት የፈጸሙትን የወንጌል ተልእኮ ስንመለከት መንፈሳዊ ተጋድሎአቸውን ለሚያስቡና ለሚደሰቱ ሁሉ በዚያ ዘመን መወለዳቸው እውነት «የተባረከ ልደት» ሊያሰኝ ይችላል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እኚህን ጻድቅ አባት በማዘከር በዓመት፫ ጊዜ ከምታከብራቸው በዓላት አንዱ የልደታቸው መታሰቢያ የሆነው ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ነው ።

እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን የሐዋርያነት ተግባር የፈጸሙትን ጻድቅ ማክበር ተገቢ ሆኖ ሳለ ፤ እኛ ደግሞ ፈለጋቸውን መከተል ፤ የወንጌል ምስክርነትን ሥራ ማድረግ ፤ የጽድቅን ተግባር መፈጸም በአጠቃላይ በተሰማራንበት ሥራ ሁሉ ተገቢ ድርሻችንን በጊዜው አከናውነን መገኘት እጅግ ያስፈልጋል ። «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ፤ ጌታ ሆይ ፤ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም ።» (ማቴ ፯ ፳፩ ) ተብሏልና ፤ የጻድቃንን ሥነ-ምግባርና ትሩፋት በማድነቅና በማውራት ብቻ እነርሱ የተጐናጸፉትን ጽድቅ ልናገኝ አንችልም ። ስለዚህ የጻድቁን ዋጋ ለማግኘት የጽድቅ ሥራ መፈጸም ይገባል ።

ተስፋዬ ረጋሳ



# ገዳም መርጃ ? ወይስ መረጃ ?

የገዳም ሥርዓት ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የተለየ በመሆኑ በገዳም ለመኖር አስቀድሞ መላ ሕይወትን ለእግዚአብሔር ማስገዛት የዚህ ዓለም ኑሮ እንዳያሸንፈው ሌሊት በጸሎት ቀን በስግደት እግዚአብሔርን ማሰብና መለመን ነው።

ከዚህም ሌላ ቤተሰብ የሌለው ሰው ሀብት ንብረት ቢኖረው ለገባበት ገዳም በመስጠት ሠርተው መብላት የማይችሉ ደካማዎች እንዲረዱበት በማድረግ ከአስፈለገም ለገዳሙ መርጃ እንዲሆን የገዳሙን ሥርዓት ተከትሎ ያከብራል ።

የገዳም ሥሪት ሁለት ዓይነት ነው ሀ/የንፍሮ ገዳም ለ/የሕግ ገዳም የንፍሮ ገዳም በመነኮሳት አንድነት የሚተዳደር ነው።

ቤተክርስቲያኑ ከመነኮሳቱ አስተዳደር ጋር የተያያዘ ነው። የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር የሚመራው በዚያው በሊቀ ማኅበሩ ነው። አበምኔት/ ይባላል ለሴቶች ገዳም ግን እመ ምኔት ናት ይህ የገዳም ስሪት ሊሠራ የሚችለው ባንድ በገለልተኛ ቦታ ተወስና በመንፈሳዊ በተጋድሎ ሕይወቱን ያሳለፈ ጻድቅ ባረፈበት የታሪክና የሃይማኖት ቦታ ነው መነኮሳት ተሰብስበው በጻድቁ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰርተው ባንድነት እየሠሩና ባንድነት እየተመገቡ ይተዳደራሉ።ገዳሙ እየታወቀና ዝናን እያተረፈ በሔዶ ቁጥር ርስት እየተሠራበት መነኮሳቱ እያረሱና እየቆፈሩ የዕጅ ስራም እየሰሩ ይኖሩ ነበር በተለይም ብዙ መንፈሳውያን መምህራን የሚኖሩበት ስለሆነ እየተማሩና እያስተማሩ ይኖራሉ ። መነኮሳቱ ባንድነት የሚመገቡት ንፍሮ ቀቅለው ዳቢ ጋግረው ስለሆነ የንፍሮ ገዳም ይባላል ።

ለ/ ሥሪታቸውና አስተዳደራቸው የአድባራት ሁነው ሳለ በቤተክህነት ወይም በመንግሥት ስያሜ ብቻ ገዳማት የሚባሉ አሉ።እነዚህ ገዳማት የርስት ሥሪታቸውና አስተዳደራቸው እንደአድባራት ነበር። ከአድባራት የሚለዩት ግን ቆሞሳት ብቻ ስለሚያስተዳድሯቸው ነው። የሕግ ገዳማት ያልናቸውም ገዳማት ተብለው እንዲጠሩ ከባለሥልጣን ከመታዘዙ በቀር በገዳማት ሥርዓት ስለማይመሩ ነው።

በ፫ተኛው መቶ ዓመት የገዳም ኑሮ ሲቆረቆር ሕግና ሥርዓቱ በሥራ ሲጀመር ይህን የተቀደሰ ኑሮ የመሠረቱት አበው መነኛና መድረሻ አድርገው የተከተሉት ሀ/ራስን ዝቅ አድርጎ ያለ ክርክር ኅብረተሰብን ለመርዳት ፤

ለ/ፈቃደ ሥጋን በፈቃደ ነፍስ ብቻ ገትቶ ከራስ አብራክ ሳይሆን ከሌላ አብራክ የተከፈሉትን ዘሮች ለማገልገል ፤

ሐ/ይህ የጣመ ነው ይህ የላመ ነው ብሎ ለሥጋ ማደንደኛ ለፍትወት መጠገኛ ከሆኑት ሀብቶች ሁሉ ተገልሎ ራስን ለሌሎች ሰውቶ በፈቃድ ደሃ መሆን እንደነበረ የገዳማቱ ሥርዓት በጉልሕ ይመሰክራል ።

በዚህ መሠረት ይህንን ቅዱስ ዓላማ ተከትለው ዓለም በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ጥበብ የምትመካባቸው ታሪካውያን ቅርሶችን ያተረፉ አያሌ መነኮሳት እንደሆኑ በዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክም ሆነ በአገራችን የገዳማት ታሪክ ግልጥ ነው ።

ይህ ቅዱስ ዓላማ እየተረሣ በአንዳንድ ቦታ እንደሚታየው ሁሉ የምንኩስናን ሥርዓት አዛብቶ በጊዜያችን የአንዳንድ መነኮሳትን አቋም ስንመለከት የገዳሙ ሥርዓት እየተዛባ የሔደ ይመስላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ይጠቅማሉ ተብለው የታመነባቸው በተለዩና በተመረጡ ቦታዎች የተገደሙት ገዳሞች እየደከሙ የነበራቸው መንፈሳዊ ጸጋና ልዩ ረድኤት እየተቀነሰ ገዳሙ ይረዳባቸው የነበሩ ሀብቶች እየጠፉና እንዳልነበሩ በመሆን በአንዳንድ ቦታ ሲታዩ ከረጂነት ወደተረጂነት ደርሰው እንመለከታለን ።

በመሠረቱ ገዳም ማለት አንድ የተለየ ክልል ቦታ ይሁን እንጂ የተመረጡ ማለት ለሥራ በመንፈስ የሚቃጠሉ ለዓለማቸውም ብቁ የሆኑ ለሚጠብቃቸው ችግርና ልዩ ልዩ ፈተና ሳይበገሩ ጽኑ በሆነ መንፈሳዊ ተጋድሎ ድልን ለመጐናጸፍ የሚኖሩበት ልዩ ቦታ እንጂ የዓለሙን መውጣት መውረድ ጥሮና ግሮ መኖር ሞክረውም ሆነ ገና ሳይሞክሩ በመፍራትና በመስነፍ ገዳሙን ገብቼ አልቀመጠውም ! በሚል የሕገ ወጥነትና የደከመ አሳብ ይዘው ከገቡ በኋላ ለጊዜው ዓላማ ያለው በመምሰል የሚዋትቱ ሰዎች መኖሪያና መጠጊያ አይደለም ።

ገዳሞች ሥነ ሥርዓታቸው ሳይፈርስ እንዲኖሩ ካስፈለገ አንዳንድመጥፎ ግብር የሚፈጽሙ ሰዎችን በመቀበል ወይም በመወከል የገዳሙ ስምና ሀብት መጥፋት የለበትም ።

ወደገዳም የሚሔዱ ሰዎች እናትና አባታቸውን እኅቶቻቸውንና ወንድሞቻቸውን በጠቅላላው ከዓለሙ የሥጋዊ ፍላጐት ርቀው ሰውነታቸውን ብፅዓት አድርገው ለእግዚአብሔር በመስጠት በአትሕቶ ርእስና በምናኔ በትምህርት አገርን ከልዩ ልዩ ጉዳት በሚጠብቅ ሰብአዊ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በመልአካዊ ባሕርይ በጸሎትና በስግደት ተወስነው በዓት አጽንተው ራሳቸውን በመግዛት ለሌሎች ምሳሌ በመሆን በፍቅረ

ተከታዩ ወደ፲፯ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት

# ሠርቶ መኖር

ዓለም ተፈጥራ የሰው ሕልውና ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ያለው በተሰጠው የማስተዋል ኃይል በመጠቀም በአካባቢው የሚፈጸሙትን ድርጊቶች በየዕለቱ ይከታተላል። ከአካባቢው የቀሰማቸውን የአሠራር ዘዴዎችና የሥራ አፈጻጸም ቅደም ተከተል በተፈጥሮና በትምህርት ካገኛቸው ልዩ ልዩ ትምህርቶችና ጥበባት ጋር በማዋሀድ የዕለት ፍላጐቱንና ምኞቱን ለማሟላት በተቻለው ሁሉ እንደሚጥርና እንደሚሞክር ኑሮ እራሷ ምስክር ናት ።

«በወዝህ (በላብህ) ጥረህ ግረህ ብላ» ያለውን አምላካዊ ቃል ስንመለከት የሰው ልጅ የተሰጠውን ትዕዛዝ ለመፈጸም እንዳልቦዘነ እንረዳለን።የሙከራ መጠኑና የአሠራር ዘዴው የተለያየ በመሆኑ ግን እያንዳንዱ ግለሰብ የሚያገኘው የሥራ ፍሬ በሙከራው ልክ የተመጠነ ነው። የዕለት ኑሮውን ለማሸነፍ ለሥራ በሚሰለፍበት ጊዜ ሁሉ እምላክ ያዘጋጀለትን የተፈጥሮ ሀብት ከምችት ከችሎታውና ከሥራ አፈጻጸም ጥበብ ጋር በማስተባበር የሥራ ውጤትን ያገኛል ። ያላወቀ ያልቻለ ያሠራር ዘዴው ያልተገለጸለት ደካማ ፍጡር ግን ሠርቶ መብላትንና መኖርን እንደ ሸክም ይቆጥረዋል ። በመንፈሱ ውስጥ መንፈሳዊ ቅናትያልተፈጠረበት ደካማ በመሆኑ በሥራ ውጤቱ ለምን እንዳልተደሰተ ለምን እንደፍላጐቱ እንዳላገኘ አይመራመርም ። የሥራ አፈጻጸም ጉድለቱ ከምን ላይ እንደሆነ ለማወቅ መንፈሱ እያነሳሳውም። እራሱን በራሱ ያደከመ ያፈዘዘና ያደነዘዘ በመሆኑ የሥራና የውድድር ዓለምን ትቶ ለመቀበል እጁን ይዘረጋል ። በሌላው አንጻር የተመለከትን እንደሆነ የኑሮ ትርጉም የገባው ትጉህ ሠራተኛ ለመኖር መሥራት እንዳለበት ስለሚያውቅ ባካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት እንደፍላጐቱ ከመጠቀም ወደኋላ አይልም ። የሥራ ውጤቱን ለማሻሻልና ለማሳመር ጽኑ ፍላጐት ያለው በመሆኑ ሥራን ለማከናወን አንድ መንገድ ብቻ አለ ብሎ አያምንም ። ብዙ መንገድ አለ ብሎም ባልሆነ መንገድ ለመሥራት አይሞክርም ። የተስተካከለ ሚዛናዊ ፍርድ በማድረግ ቀናውን መንገድ ይከተላል እንጂ ፤ በጥረቱ በልፋቱና በየዕለቱ በሚያደርገው ሙከራ ሠርቶ ለመኖር በመፈለግ ለራሱም ሆነ ለመጪው ትውልድ ብዙ የሥራ ቅርስ ትቶ ያልፋል ። በዚህም ዓይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ ከመጡ የሥራ ዓይነቶች አንዱና ዋናው የመኖር ዋልታ የእርሻ ሥራ/ ግብርና/ ነው።

በልዩ ልዩ የሃይማኖትና የሳይንስ መጻሕፍት እንደተገለጸው የእርሻ ሥራ ጥንታዊነት ያለው ሆኖ የቆየ እንደመሆኑ መጠን የሥራው ዓይነትና የአሠራር ዘዴው የአሠራር ሥነ ሥርዓትን የተከተለ ነው።

እንግዲህ እርሻ ማለት ምን እንደሆነ ለመግለጽ እንሞክራለን እርሻ በዕፀዋትና በእንስሳት የተፈጥሮ እስተዳደግ ሥነ ሥርዓት የተመሠረተ የሥራ ዘርፍ ነው።

እንደሥራ መቆጠሩ አስፈላጊ የሆነው የሰው ጉልበትና ሀብት ወጥቶበት ውጤት በማስገኘቱ ሲሆን እንደሌላው ሥራ ዓይነት ሁሉ ሠራተኛው እንዲጠቀምበት ቢሻ ገቢው ከወጪው መብለጥ አለበት ። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ገበሬ በእርሻ ለመጠቀም ከፈለገ ለእርሻ ሥራ የሚጠቀምባቸውን ዕፀዋትና እንስሳት በተፈጥሮ ያገኙትን የሕልውና ጠባይ ሳያዛባ፤ በሚፈለግበት ጊዜና ቦታ በተስማሚው የተፈጥሮ አካባቢ ላይ በመዝራት ወይም በማርባት የፈለገውን የእርሻ ውጤት ይሰበስባል ። ገበሬው የእንስሳትንና የዕፅዋትን ዕድገት በመቆጣጠር እንደፍላጐቱ ለግል ጥቅሙ ሊያውላቸው ከቻለ የእርሻ ሥራን አከናወነ ይባላል። የመቆጣጠር ኃይሉና ችሎታው እየተሻሻለና እየነጠረ ሲሄድ በእርሻው የሚያገኘው ጥቅም እየዳበረ ይሄዳል እንግዲህ የገበሬው ምርት ወይም የርሻ ውጤት የሚወሰነው በእንስሳትና በዕፀዋት የተፈጥሮ እድገት ላይ ባለው የመቆጣጠር ችሎታ መሆኑን ከተረዳን በጥንታዊና በዘመናዊ የርሻ ዘዴ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ አያስቸግረንም ። አንድ በዘመናዊ አቅዋም የደረጀና ሌላ ጥንታዊ አያያዝ ያለውን እርሻ ወስደን ብናወዳድር በመሀከላቸው ያለው ዓቢይ ልዩነት የሚፈጠረው ገበሬው ለእርሻው በሚጠቀምባቸው እንስሳትና ዕፀዋት እድገት ላይ ባለው የቁጥጥር መጠን ወይም ችሎታ ነው ቢባል ሐሰት አይሆንም ። በጥንታዊ ዘዴ የሚያርሰው ገበሬ ተፈጥሮ በሰጠውና በአደራጀለት የሀብት ክምችት ማለት ዝናብ አፈርና የዘር ዓይነት ይተማመናል ። የሚሰማው የሥራ ሃላፊነት መሬቱን አርሶና አለስልሶ ለዘር ማዘጋጀት ሲሆን የምርቱ መጠን ይወሰናል ብሎ የሚያምነው ፈጣሪ በሚያደርግለት አምላካዊ ችሎታ ብቻ ይመስለዋል ። ሠርተህ፤ለፍተህ፤ግስነህ ብላ ያለውን አምላካዊ ቃል የዘነጋ ባይሆንም ፈጣሪው የሰጠውን የማመዛዘንና የማስተዋል ችሎታ በማስተባበር የተሰጠውን የተፈጥሮ ሀብት ክምችት እንዳለ በመጠቀም ፋንታ ሊያሻሽለው የጐደለውን ሊያሟላ ይገባዋል። እንዲህም ማለት በጊዜው የሚጠብቀው ዝናብ በርሻው ላይ ያለው የአፈር ሁኔታና ከምርቱ አትርፎ ያከረመው ወይም የሸመተው ዘር የሰጠውን ምርት እንደሰጠው ይጠቀማል እንጂ እነዚህን የተፈጥሮ ሀብቶች አስተባብሮ ከእርሻ ላይ ጥቅምን ማግኘት ሲሻ በየዓመቱ የሚያገኘው ምርት ለምን እንደሚጨምርና እንደሚቀንስ ለማወቅ ቢጣጣርም ሁኔታውን ለማሻሻል የሚያደርገው ሙከራ አጥጋቢ አይሆንም ። በጠቅላላው አነጋገር የማግኘቱንና የማጣቱን ሁኔታ ይወስነዋል ብሎ የሚያምነው የፈጣሪው ቸርነትና አስተያየት እንጂ የተጓደለውን ባለሟሟላት ዝግጅትን ባለማሣመሩ የተሰጠውን ቀዋሚ የሥራ ትዕዛዝ መሠረት እርሻዬ እንደ ሥራዬ ከፈለኝ ብሎ ይጽናና ዘንድ ሕሊናው እያደፋፍረውም ። የሚጠቀምባቸው የአስተራረስ ዘዴዎች ከሞላ ጐደል ከቀዳሚ ገበሬዎች የተወረሱ እንጂ ጊዜውን በመከተል አስፈላጊ ለውጥ ያልታየባቸው ናቸው ። ይህም ሲባል የጥንታዊው ገበሬ የአስተራረስ ዘዴው ጠቃሚ አይደለም ለማለት ሳይሆን ያለውን የእርሻ አቅዋም በመጠኑ ሊያሻሽል እንደሚገባው ለመግለጽ ነው። በእርግጥ የጥንቱ ገበሬ ኃይለኛ ሠራተኛ እንደሆነ ማንም አይክድም ። የልፋቱንና የድካሙን ዋጋ ግን የእርሻ ሥራው ባጥጋቢ መልክ እንደማይከፍለው ለማንም ግልጽ ነው ።

በእርሻ ሥራው ተጠቃሚና አትራፊ የሆነውን ገበሬ የወሰድን እንደሆነ እንዳሉ ባገኛቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ብቻ ሲተማመን አናየውም ። ዝናብ ቢጠፋ በመስኖ የአፈር ልምላሜነት ቢቀነስ በማዳበሪያ ዘር ቢመርጥ በዘመናዊ ዘዴ የተሻሻለውን ምርጥ ዓይነት እንደሆነ እንረዳለን ። በሽታና የእህል ተባይ ቢመጣበት የሚከላከልበት ዘዴ አለው ። በሽታውና ተባዩ ከመምጣቱ በፊት መነሻ የሆኑ ምክንያቶችን ከማገለል አይቆጠብም ። እንደ አስፈላጊነቱ እያየ ውርጪና ልዩ ልዩ የእህል በሽታዎችን ሊቋቋም የሚችል ምርጥ ዘር ይጠቀማል እንዲህ ዓይነቱ ሙከራ በአዝርዕት ብቻ ሳይወሰን በቀንድ በጋማ ከብትና በመሳሰሉት የእንስሳት እርባታዎች ሁሉ እንደአስፈላጊነቱ ይፈጸማል ።

በዚህ ሁኔታ ሠርቶ ለመኖርና ለመጠቀም ወደኋላ አይልም። ለእውነተኛ ገበሬ ሳይሠራ መብላት ሳይዘራ መሰብሰብ የኑሮ ዓላማው አይደለም የብርቱ ገበሬ ምርት ለዕለት ጉርስ ፤ ልብስና የመንግሥት አሥራት ብቻ አይወሰንም። ከራሱ አልፎ በሌላው የሥራ ዓለም ለተሰለፉት በላተኞች ይተርፋል በእርሻ ውጤት ተማምነው ለተቋቋሙ እንዱስትሪዎች የተፈለገውን የርሻ ሀብት በዝግጅት ያቀርባል ። የሀገር ገቢያ ፍላጐቱን በማሟላቱ ሳይወሰን የተረፈውን ምርቱን ለውጪ ንግድ በማቅረብ የአገሩን የገንዘብ አቅዋም ያጠነክራል ። ይህ ሁሉ ልፋትና ጥረት ገበሬው ሠርቶ ለመኖር ሠርቶ ለመጠቀም ስንፎ ሳለማስቸገር «ስርተህ፤ለፍተህ ፤ በወዝህ በላብህ ብላ» ያለውን ቀዋሚ የአምላክ ትእዛዝ ለማሟላት ሊሠራ ቢፈልግ ብዙ ምርጫ እንዳለው ያስረዳል ።

ከአንድ የእርሻ ምሁር የተዘጋጀ
አቅራቢ በለጠ አበበ ፤

# ገዳም መርጃ? ወይስ ...?

ከ፲፭ኛው ገጽ የዞረ

ንዋይ ሳይገዙ ለተለየ ጥሪ ሳይቃትቱ የሚኖሩ መሆን አለባቸው።

ይህን ዓላማ ስተው የራሳቸውን ጥቅም ለማሳደድ በአንዳንድ ቦታ እየተዘዋወሩ ሥርዓትና ደንብን ባህልና ሃይማኖትን ባልሆነ ቦታ ሲያቋሽሹ የሚታዩትንም መነኮሳት ብለን ልንጠራቸው አይገባም።

የገዳሞቻችን ባህልና ሥነ ሥርዓት በሚገባ ተጠብቀውና ተከብረው እንዲኖሩ በነዚህ ገዳሞች የሚኖሩት መነኮሳት በጸሎት ብቻ ሳይሆን ባህላችን እንዳይዘነጋ ብራና ፍቀው ቀለም በጥብጠው መጻሕፍትን በመጻፍና በመደጐስ ልዩ ልዩ ሥዕሎችን በመሳል የጥራዝና የቱታን ጥበብ በማፍለቅ በቅርፃ ቅርፅ ኪነ ጥበብ በመራቀቅ ከዚህም አልፈው ተርፈው ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸውን መዝሙሮችና ጸሎቶች በመድረስ እንዲያዘጋጁ ያስፈልጋል ።

እንዲያውም ለአካባቢው ሕዝብ የግብርና ሞያ አርአያ ለመሆን በአካባቢያቸው የሚገኙትን ጠፍ ቦታዎች ልዩ ልዩ አዝርእትና አትክልትን በማዝመር ራሳቸውን በቀላል ኑሮ ሸንግለውሌሎችን ይጠቅሙ እንደነበር ሕያው ታሪካቸውና ስማቸው በየምዕራፉ ይመሰክራል ዛሬም ያሉት ቢሆኑ የእነዚህን አርአያ መከተል ይኖርባቸዋል ።

እንግዲህ ገዳማዊው መመኪያችን በውስጡም የሚገኙት ባህልና ሥርዓታችን ከዚህ ከደረሰ ለተተኪው ትውልድ ውል የሌለው ቋጠሮ አድርገን ማቆየት የለብንም ።

ይህ ባህልና ሥርዓት ላለፈው ትውልድ ወይም በጊዜያችን ለሚገኙ አንዳንድ ግዴለሾች ቀላል መስሎ ቢታይ ለተተኪው ትውልድና ዛሬም ጥቅሙን ለሚያውቁ ሁሉ የሚታመንበት ከፍ ያለ ቅርስ ስለሆነ ሁሉም በየበኩሉ ቢያስብበት የተሻለ ነው ።

ዛሬ በአንዳንድ ገዳማት እንደምንመለከተው« ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» የሚለው ቃል ተዘዋውሮ የሚቀበል እንደብፁዕነት ተቆጥሮ ለሥራ የሚዘረጉ እጆች እየቀነሱ ለመብልና ለምፅዋት የሚዘረጉ እጆች እየበረከቱ ሔደዋል ።

ታዲያ በአካባቢው ያሉትን መሬቶች በማልማት ልዩ ልዩ ተግባረ ዕድን በመሥራት ራሳቸውን የማይረዱ ሆነው ከተገኙ የምንኩስና ሥነ ሥርዓት መርጃ እንጂ መረጃ አለመሆኑን ያመለክታል ።

ስለዚህ የገዳም ሥርዓት ሌላውን ለመጥቀምና ለሌላው መልካም አርአያ ለመሆን የተቋቋመ ስለሆነ በገዳም የሚኖሩ መነኮሳት የሌላውን እጅ በመመልከት መላ ዕድሜያቸውን የሚገፋ ከሆነ ከዓለማዊ ኑሮ የተሻለ ሆኖ ስለማይታይ ከመረዳት መርዳትን ከመቀበል መስጠትን እየተለማመዱ የገዳሙን ሥነ ሥርዓት ቢያከብሩ ተተኪው ትውልድ እንደሚከተላቸው እናምናለን።

ነቅዓ ጥበብ ወንድም





www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ

(ከከፍያለው መራሂ)

## ሥርዓተ ጋብቻዎን በቤተ ክርስቲያን ማድረግ ይወዳሉ ?

ብዙ ጊዜ ሰዎች እንደ ባሕላቸውና ሥርዓተ ማኅበሩ ለሥርዓተ ጋብቻ የተለያየ ትርጉም ፣ ዓላማና አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል ። ያም ሆነ ይህ ጋብቻ ሲባል ጠቅላላ መንፈሱ ኅብረትን ፣ አንድነትንና ውሕደትን ያሳያል ። በዚህ ጽሑፍ የተፈጥሮ ሕግን ከክርስትና ሕይወት ጋር በማገናዘብ የጋብቻን ትርጉምና ዓላማ ለሰዎች ሁሉ በተለይም ለክርስቲያን ወገኖች ለማስረዳት እንሞክራለን ።

እንግዲህ የጋብቻ መሠረታዊ ፍልስፍና ከብቸኛነት ወደ ኅብረት ፣ ከተነጣጠለ ሕይወት ወደ ውሕደት ስለሆነ ፣ የጋብቻ ትርጉሙ በአጭር ዐረፍተ ነገር « ሕይወትን መካፈል » ማለት ነው ። እንደሚታወቀው ሁሉ የዚህ ዓለም ተፈጥሮ አቀበትና ቁልቁለት ፣ ተራራና ሜዳ ፣ ወዘተ ... የበዛበት እንደመሆኑ መጠን ያችም ሕይወት መራራና ጣፋጭ ፣ መከራና ደስታ በየጊዜው የሚፈራረቁባት የሰዎች የኑሮ ጠባይ ናት ። እንግዲህ «ሕይወትን መካፈል » ሲባል መራራውን ትቶ ጣፋጩን ፣ መከራውን ትቶ ደስታውን ሳይሆን በመራራውም ሆነ በመከራው መረዳዳት ነው፤ ስለዚህ ለክርስቲያኖች የሕይወታችን መመሪያ እንዲሆን የተሰጠን መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይመክረናል ። ወደ ኋላ መለስ ብለን የስነ ፍጥረትን ታሪክ ስንመለከት አባታችን አዳም ፣ እናታችን ሔዋንን አርቆ ሳይሆን አቅርቦ ፣ ይቺ ከሥጋዬ የተገኘች ሥጋዬ ፣ ከአጥንቴ የተገኘች አጥንቴ ናት ሲል «ሕይወቴ » ብሎ እንደጠራት ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል ። ይህም ከጎኑ አጥንት የተገኘች ግማሽ ሕይወት መሆኗን ያስረዳል ብዙ ሊቃውንት ጋብቻን በተለያዩ ምሳሌዎች ያስረዳሉ ። ጋብቻ አንድ መሠረታዊ አስተያየት ሰጥቶናል ። « ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፣ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ። » ይህ አንድ ሥጋ የተባለው አነጋገር አንድ አካል በሚለው አነጋገር ሊተረጎም ይችላል ። ይህ በጋብቻ የተዋሐደው አካል ሁለት መሠረታዊ ብልቶች አሉት ። እነርሱም « ራስና ልብ » ናቸው ። ባልን በራስ ፣ ሚስትን በልብ መመሰል ይቻላል ። እነዚህም ሁለት ብልቶች በጋብቻ ለተሣሠረው አካል አስፈላጊ በመሆናቸው ይህ አካል ያለ ራስ ወይም ያለ ልብ መኖር አይችልም ፣ ለማንኛውም ሕይወታዊ አካል አንድ ራስ ፣ አንድ ልብ እንጂ ሁለት ራስና ሁለት ልብ እንደማያስፈልጉት ሁሉ ባልና ሚስትም አንድ አካል እንጂ ሁለት አካላት ሊባሉ እንደማይገባ ግልጽ ነው ።

እንግዲህ ከሞላ ጐደል የጋብቻን ትርጉም ከተረዳን ዓላማውስ ምንድን ነው ? በእርግጥ ማንም ሰው ለሕይወት የተለያየ ትርጉም እንደሚሰጣት ሁሉ ፣ ለዚህም የተለያየ አገላለጽና አመለካከት ሊኖረን ይችላል ፣ ሆኖም የጋብቻ መሠረታዊ ዓላማዎች ፈቃደ ሥጋን መፈጸም ፣ በማኅበራዊ ኑሮ መረዳዳትና ዘር መተካት መሆናቸው ለማንም ሰው ግልጽና የወል ሀሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ ብለን እንገምታለን ። በእርግጥ ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ መመገብና መራባት የተፈጥሮ ሕግ መሆናቸው እንደማይካድ ሁሉ ከሕጋዊ ጋብቻም ደግሞ ልምላሜና ፍሬ ይጠበቃል ።

እንግዲህ በእውነተኛ ፍቅርና እምነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ ሁለቱም ወጣቶች ሕይወትን በእኩልነት መንፈስ ይካፈላሉ ፣ በመካከላቸውም በጎ መተሳሰብ ይኖራል ። አንድ አንድ ሰዎች ሲናገሩ ፣ አያሌ ጋብቻዎች ትርጉም የሚያጡትና አስልች የሚሆኑበት አንዱ ምክንያት በትዳር ጉዳይ ሴቶች የእኩልነት መብት እንዳይኖራቸው የወንዶች መጋፋት ነው ይላሉ ። አንድ ደራሲ ሲናገሩ ፣ « አንተ የሚስትህ ራስ ለመሆን የምትችለው አገልጋይዋ ለመሆን በምትፈቅድበት መጠን ነው » ይላሉ ። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ሲወዳት ከፍቅሩ የተነሣ ራሱን አሳልፎ እስከመስጠት እንደደረሰላት ሁሉ ፣ ባሎች ደግሞ ሚስቶቻቸውን ራሳቸውን እስኪለውጡላቸው ድረስ ሊወዷቸው እንደሚገባ ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ ጽፎልናል ። ስለዚህ ራሱን ስለሚስቱ ከመለወጥ በላይ ምን ነገር ይኖራል። ? የወንዶችስ የሴቶችን እኩልነት መብት መጋፋት ከምኑ ላይ ይሆን ? በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ ያሉ ባልና ሚስቶች ያላቸው ፍቅር በእምነት ላይ እንጂ በወረት ላይ የተመሠረተ ሊሆን አይገባውም ። እውነተኛ ፍቅርና እምነት ደግሞ መከባበርን መለባበስንና መተሳሰብን ያስከትላል ። ይህ እንግዲህ ጣፋጭ ሕይወት ያለው የጋብቻ መሠረት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ወጣቶች ሥርዓተ ጋብቻን በቤተ ክርስቲያን በተክሊል ለመፈጸም ትእዛዙንና ሕጉን፣ ቃለ መሐላውን ሲቀበሉ ፣ «ከሥጋው ጸመኛ ነኝ » እንዲሉ ቅዱስ ቁር

ተከታዩ ወደ ፳ኛው ገጽ ዞሯል



# ድንግል በቤተ ልሔም

የመጀመሪያው ፍጡር አዳም ከፈጣሪው የተሰጠውን ትእዛዝ በመጣሱ ከኃጢአት አዘቅት ወድቆ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ከኖረ በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ በሰጠው ተስፋ መሠረት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማየት ወርዶ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ ተወለደ ።

ይህም ከአምስቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ምስጢረ ሥጋዌ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው ።

ቅድስት ድንግል ማርያም ወልደ አምላክን በፀነሰችበት ወራት በጊዜው ነግሦ የነበረው አውግስጦስ ቄሣር ባወጣው ትእዛዝ መሠረት የሀገሪቱ ሕዝብ ብዛት ይታወቅ ዘንድ ሰው ሁሉ ይቆጠር የሚል ትእዛዝ ስለነበር እንዲጠብቃት አደራ ከተሰጠው ከዮሴፍ ጋር እመቤታችን ፀንሳ ሳለች ሊቆጠሩ ወደ ቤተ ልሔም ሔዱ ።

በዚያም እያሉ የምትወልድበት ቀን ስለደረሰ ሰማይና ምድር የማይወስኑትና ሊሸከሙት የማይችሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በከብቶች በረት ታህሣሥ ፳፱ ቀን ተወለደ እንደ ልጆችም ተጠቀለለ ጊዜውም የውርጭ ወራት ነበርና አህያና ላሞች በእስትንፋሳቸው አሟሟቁት ይህንንም አባ ሕርያቆስ የተባለው ሊቅ « ወአስተማወቅዎ እስትንፋስ እድግ ወላሕም በመዋዕለ ቁር ። » ብርድ በጸናበት ጊዜ ላምና አህያ በእስትንፋሳቸው አሟሟቁት ብሏል ። ቅዳሴ ቁ- ፩፪፳፫

መላእክት « ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ሰላም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ » እያሉ ዘመሩለት ለእረኞችም ስለአበሰሩአቸው እረኞችም በደስታ ጨፈሩ የዱር አራዊት ሳይቀሩ መድኅን ክርስቶስ ተወለደ በማለት በቋንቋቸው ፈነጠዙ ኢሳይያስም ቀደም ሲል በትንቢቱ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበርና « በሬ የገዛውን አህያም የጌታውን ጋጥ አወቀ እስራኤል ግን አላወቁኝም ሕዝቤም አላስተዋለኝም » ት/ኢሳ ም- ፩ ቁ- ፫ ።

ሰብአ ሰገልም ከሩቅ ምሥራቅ በኮከብ እየተመሩ መጥተው ለሄሮድስ ዜናውን ሲነግሩት ተደናግጦ ካገኛችሁት ንገሩኝ እኔም እንድሰግድለት ብሎ እነርሱን ከሸኘ በኋላ እንደገና ከመማክርቱ ጋር በሕፃኑ ላይ ያደረገውን ሴራ በዓይነ ሕሊናችን እናስታውሰዋለን ።

ሰብአ ሰገልም በኮከብ ተመርተው ከቦታው ሲደርሱ ሕፃኑንና ድንግል ማርያምን አይተው በጣም ደስ አላቸው ከግመሎቻቸው ወርደውም መላልሰው ሰገዱለት ይዘውት የመጡትንም እጅ መንሻ አገቡለት በሌላ በኩል እን እመቤታችን በብዙ ምሳሌዎች እንደምትመሰል መጻሕፍት ይናገራሉ ። ከነዚህም ምሳሌዎች መካከል ፣

ሀ/ ቤተልሔም የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው

ይህም ቤተ ልሔም ማለት የኅብስት ቤት ማለት ነው የኅብስት ማደሪያ እርሷ ናትና ።

ለ/ ኤፍራታ ትባላለች ኤፍራታ ማለትም ፀዋሪተ ፍሬ ማለት ሲሆን እግዚአብሔር ወልድን በማህፀንዋ ተሸክማለችና ።

ሐ/ ከብታ ትባላለች የዚህም ትርጉም ቤተ ሰብሐት ማለት ነው እመቤታችን ምስጋና ገንዘቡ የሆነ ፈጣሪ ሰማያት ወምድርን ተሸክማለችና ይላል እነዚህንም ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጂ ሌሎችም ብዙ ምሳሌዎች እንዳሏት መጻሕፍት ይናገራሉ ።

የክርስቶስ ልደት እንደሚታወቀው ሁሉ የአዳምን ልጆች በጠቅላላ ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ አውጥቶ በእግዚአብሔርና በሰዎች ፣ በሰዎችና በሰዎችም መካከል ከጠቅላላው ሥነ ፍጥረት ጋር ከነበረው ጥል አስታረቀ «በጨለማ ላሉ ብርሃን ወጣላቸው » ብሎ በወንጌል እንደተጻፈው በእርሱ ከመቤታችን መወለድ ብርሃን ወጣልን ።

ድንግል ማርያም በቤተ ልሔም በከብቶች በረት የበኩር ልጅዋን ስትወልድ ሐኪም ፣ ወይንም ነርስ ሌላው ቀርቶ የመንደር አዋላጆች እንኳን በአጠገቧ አልነበሩም እንደ አራሶች ለወገቧ መጠገኛ አጥሚት የሚያዘጋጅላት እንኳን በአጠገቧ አልነበረም ወይንም ገንፎ የሚያገነፋላት አንድስ እንኳ አልነበረም ።

ነገር ግን የወለደችው ፍጡር ሳይሆን ፈጣሪ ፣ ሰው ሰራሽ መድኃኒት የሚያስፈልገው ሳይሆን ራሱ የዓለም መድኃኒት ፣ የተገኘ ሳይሆን ራሱ ዓለሙን ያስገኘ አምላክ ወሰብእ ስለሆነ ማህተመ ድንግልናዋን ሳይለውጥ ስቃይ መከራ ሳያገኛት አንሱኝ አስተኙኝ ሳትል ድንግል ወእም ድንግልናን ከእናትነት አስተባብራ ተገኝታለች ። ከሴቶች ወገን በሆንችው በሔዋን ወደ ዓለም የገባው ኃጢአትም በመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ምክንያት ደግሞ የዓለም ድኅነት በቤተ ልሔም ተገኝቶልናል ።

ስለዚህም እኛ ሴቶች ከሌላው በለጠ እንመካበታለን እርሷም « ምክ ሆን ለደናግል » በሚል ቅጽል ትጠራለች ድንግል በቤተ ልሔም ለቆጠራ እንደወጣች በዚያው በከብቶች በረት የወለደችው የክርስቶስ ልደት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የምናከብረው ሳይሆን ሁልጊዜ በየዕለቱ በየሰዓቱ በአእምሮአችን ባለማቋረጥ የሚፈልቅ የደስታ ምንጭ ነው ። ድንግል በቤተ ልሔም መድኅን ክርስቶስን ባትወልድ ኖሮ ገነት ምድራችንን አናገኛትም ነበርና ።



www.ethiopianorthodox.org

# የበቆሎ እንጀራ አገጋገር

በቆሎውን በደንብ ለቅመው ይሸክሽኩት ከሸከሸኩ በኋላ ገለባውን አበጥረው በደንብ ፀሐይ እንዲመታው ያደርጉ ከደረቀ በኋላ ወፍጮ ቤት ወስደው ያስፈጩት ።

ዱቄቱ ተፈጭቶ ሲመጣ በጥሩ ወንፊት ይንፉት ከዛም የሚበቃዎትን ያህል ዱቄት መጥነው ማለትም እንደ ቤተሰበዎ ብዛትና ማነስ በወፍራሙ በሙቅ ውሃ ያቡኩት ግን ሲያቦኩ ሊጡን እንዳያቀጥኑት ይጠንቀቁ ጥቅል አቦካክ እንዲሆን ያስፈልጋል ።

በማግስቱ የተቦካውን የበቆሎ ሊጥ አራት ቦታ አስተካክለው ይክፈሉት ከተከፈለ በኋላ አንድ አራኛውን ማለትም ከአራቱ ክፍልፋይ ሦስቱን ትተው አንደኛውን ክፋይ ብቻ ለአብሲት ያድርጉት አብሲቱ ከገባ በኋላ የገባው አብሲት በረድ ሲል ሊጡም ኩፍ ይላል ያኔ ምጣድዎን አስምተው የተሞናሞነና የተሞናደለ ዓይኑ እንደ ማር ሰፈፍ ያማረ እንኳንስ በጥርስዎ ለማኘክ ቀርቶ በአይንዎ ሙሉ ለማየት የሚያሳሳ ጥሩ እንጀራ ይወጣዋል ።

ይህም እንጀራ ቢበላ ለጤናማም ሆነ ለበሽተኛ ሰው የሚስማማ በሆድ ውስጥ ቶሎ የሚዋሃድና የማይከብድ ስለሆነ ሁልጊዜ ያለ ብዙ ድካም ሰርቼ ለመብላት የሚያመቸኝ ለኔም ሆነ ለቤተሰቤም ለጤናችን የሚስማማ ምግብ እርሱ ነው በማለት የዘወትር ምግብዎ እንደሚያደርጉት አንጠራጠርም ። ለሁሉም ትንሽ ይሞክሩና ይቅመሱት ።

ወ/ሮ ብርሃን ተድላ ፤

# ቤተ ክርስቲያንና ...

ከ፲፰ኛው ገጽ የዞረ

ባንን ለመቀበል ይፈራሉ ። በመሠረቱ ክርስቲያናዊ ጋብቻ ከቅዱስ ቁርባን ውጭ እንዲሆን ሕገ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድም ። « ልማድ ሲገነ ግን እምነት ይሆናል » እንዲሉ በክርስትና እምነት ተደጋፊነት የሌለው የልማድ አስተሳሰብ ብዙ ሰዎች ዕድሜያቸውን መወሰን ይችሉ ይመስል የወጣትነት ዘመናችንን ስንፈጽም ቅዱስ ቁርባንን እንቀበላለን በማለት ጊዜያቸውን በዋዛና በፈዛዛ የሚያሳልፉ አሉ ። በመሠረቱ ለማንኛውም ክርስቲያን ከጌታ ማዕድ ለመሳተፍ ረዥም ቀጠሮ ከቶ አያስፈልገውም ። ቅዱስ ጳውሎስ እነሆ የመዳን ቀን ዛሬ ነው ይላል ።

ቅዱስ ቁርባን ለአረጋውያን እንጂ ለወጣቶች አይገባም እንዳንል መጽሐፍ ቅዱስ « በወጣትነት ዘመን ፈጣሪህን አስብ » ይላል ። እንደዚሁም « ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ » ሲል ወደ ጌታ ለመቅረብ የዕድሜ ገደብ እንደማያስፈልግ ታላቁ መጽሐፍ ያረጋግጥልናል ። በሕገ አሪት እንደምናነበው ለመሥዋዕትነት የሚገባው ቀንዱ ያልከረከረ ጠቦት እንጂ ያረጀያፈጀ እንዳልሆነ ፤ ግልጽ ነው ። ስለዚህ ክርስቲያን ወጣቶች ሕጋዊ ጋብቻቸውን በቅዱስ ቁርባን እንዲያደርጉ ምንጊዜም የቤተ ክርስቲያን ምክርና ትምህርት ነው ።

አንዳንዶች ደግሞ በቅዱስ ቁርባን አግብተን በኋላ እርስዋ ወይም እኔ ብሞት ምን እንሆናለን ? ብለው ይጨነቃሉ ። ለዚህም የቤተ ክርስቲያናችን የሕግ መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥት « ባልዋ ወይም ሚስቱ ከሁለት አንዱ ቢሞት እንደገና ቁርቦ ያግባ ወይም ታግባ » ይላል ። እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ፤ ሥርዓትና ትምህርት እንደዚህ ከሆነ ክርስቲያን ወጣቶች በቅዱስ ቁርባን ለምን ጋብቻቸውን አይፈጽሙም ? ቅዱስ ቁርባን የሚያስፈልገውስ ለነማን ነው ? ሐዋርያው ጳውሎስ «ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ » ይላል ። ስለዚህም ቅዱስቁርባን መንፈሳዊ ብቃት ላላቸው ሰዎች ብቻ ቢፈቀድ ኖሮ ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበል ሰው ባልተገኘም ነበር ። ቅዱሳት መጽሐፍት እንደሚያስረዱት ከሆነ በጌታ ማዕድ ላይ መገኘት የሚገባቸው መንፈሳዊ ብቃት የሌላቸው መሆናቸውን የተረዱ ብቻ ናቸው ። ለዚህም የጠፋውን ልጅ ታሪክ ማስታወስ ጠቃሚ ይመስላል፡፡ አባካኙ ልጅ በአመንዝራነት የትም ሲባዝን ኖሮ ወደ ወላጆቹ ቤት በተመለሰ ጊዜ አባቱ ሁኔታውን ልመርምር በማለት አንድ ሥርቻ ውስጥ እንዲሰነብት አላደረገውም ።ልጁን በሩቅ እንዳየው ሮጦ ሄዶ አንገቱ ላይ ተጠምጥሞ ሳመው ፤ ታላቅ ድግስም ደግሶ በአንድ ማዕድ አብሮት በላ ፤ ይህም የእውነተኛ ይቅርታ ምልክት ነው ።

እ… ግዲህ ከዚህ ወጣት ምሳሌ እንደተ…ረዳው ቅዱስ ቁርባን ለእነማን እንደሚገባ ልናስተውል እንችላለን ። በኃጢአታቸው ተጸጽተው ንስሐ ለመግባት ፈቃደኞች የሆኑትን ሰዎች ከጌታ ራት እንዲታገዱ ማድረግ ቅዱስ ቁርባንን ኃጢአት የለብንም እያሉ ለሚመኩ ወይም ደግሞ ኃጢአት ሲሠሩ ሳልተያዙ ሰዎች የተሠራ አድርጐ እንደመገመት ይቆጠራል ። ነገር ግን እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ከእውነት የራቀ መሆኑ ግልጽ ነው ። እንግዲህ አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔር ከመረጠለት የዕድሜ ጓደኛው ጋር በጋብቻ ስንሰለት ሲተሣሠር የክርስትና ሕይወቱ መድኃኒት በሆነው በቅዱስ ቁርባንጸንቶ ይኖራል ። እንግዲህ አንድ ወጣት በክርስትና ሕግ መሠረት ሥርዓተ ጋብቻውን በቤተ ክርስቲያን ለመፈጸም ሲያስብ የትዳር ጓደኛውን ለመምረጥ ከዚህ የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች በቅድሚያ ራሱን ይጠይቅ « ልጅቱ ክርስቲያን ናትን ? »«አብሬያት ክርስቶስን ማምለክና ጸሎት ማድረስ እችላለሁ » ? የሚለውን ጥያቄ በቅድሚያ መጠየቅ ያስፈልገዋል ። የባልና የሚስት በሃይማኖት መመሳሰል የመልካም ጋብቻ መሠረት ነው ፤ መልካም ጋብቻደግሞ ቤተ ክርስቲያናችን የምትደግፈውና ኅብረሰቡም የሚቀበለው ነው ።



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## በሎጂክ የተጻፈ የንግግር ጥበብ

«በሎጂክ» ያልተደገፈ የሐሳብ ማዋቅርና ንግግር ሁሉ ማሠሪያ እንደ ሌለው ነዶ ነው ብንል ማጋነን አይደለም። ከዚህም የባሰ ቅርጽ ለመስጠት ከተፈለገ አእምሮአቸው ከተነካ ወይም የወፈፍተኛነት ጠባይ ከተቆራኛቸው ሰዎች የሚመነጭ ሐሳብና በሎጂክ ሕግ ያልተደገፈ ንግግር ሁለቱም አንድ ናቸው ማለት ይቻላል ።

የሎጂክ ጥናት በቋንቋ ጥናት ውስጥ የሚገኘውን የዐረፍተ ነገር አመሠራረትና አወቃቀር ቅርጽና ይዘት የሚጠቁም የሚያመለክት /ሲሆን በስፋት በሚያመለክትበት ጊዜ ደግሞ ባጠቃላይ ሥነ ጽሑፍ—ታሪክ ሣይንስና ፍልስፍና ሌሎችም ይህን የመሳሰሉ ሁሉ የየራሳቸው ሎጂካዊ ቅንብርና አቀማመጥ ሎጂካዊም የአሠራር ስልት አላቸው። ስለዚህም የሎጂክ ትምህርት ለቋንቋና ሰዋሰው ጥናት ሕግንና ደንብን ወሣኝ ብቻ ሳይሆን ለድርሰትና ለንግግር ዋና መርሐ ግብር መሆኑን ለመገንዘብ ሰፋ ያለ ጥናት መከተል ያስፈልጋል ማለት ነው።

ከሎጂክ ውጭ የሚታሰብም ሆነ የሚነገር ወይም በጽሑፍ የሚነደፍ ድርሰት ምንም ዓይነት መነሻና መድረሻ ከቶ ዓላማም ሊኖረው አይችልም ከሎጂክ ውጭ የሆነ የሐሳብ አቀራረብ ወይም ንግግር ሁሉ ምንም ዓይነት ግብ ስለማይኖረው ተደማጭነትም ሆነ ተቀባይነት የለውም። ሎጂካዊ ማስረጃ የሌለው ንግግር ሁሉ መሠረታዊ ዓላማን በማሳት እርእስትን ለቆ ሽምጥ መጋለብን ያስከትላል። ከዚህም የተነሣ የቋንቋን ብቻ ሳይሆን የሥነ ጽሑፍን የታሪክን የሣይንስና ፍልስፍናን የመልክአ ምድርን አቀማመጥና በአጠቃላይ የሥነ ተፈጥሮን ትምህርት ሁሉ ከማበላሸት ያደርሳል ።

ለምሳሌ «ናይሮቢና ካርቱም ጥንታውያን የኢትዮጵያ ገዳማት ናቸው፣ ወይስ የኡጋንዳ፣ የሚል ጥያቄ ቢቀርብልን ከሁለቱ አንዱንም ነገር መምረጥ አንችልም ጠያቂውንም ዓላማቢስ አደናጋሪ አድርገን እንታዘበዋለን ወይም የአእምሮ ጤንነት ጐድሎታል ከማለት እንደርሳለን። ይህ እንግዲህ የመልክዐ ምድና የታሪክ ማደናገሪያ ጥያቄ ነው እንበል። ከዚህ ጋር ከሎጅክ ሕግ ውጭ ያፈነገጠ የእሐዝ (የቁጥር) ማደናገሪያም ሲቀርብ ይችላል ለማስረጃም ያህል «ሁለትና ሶስት ፪+፫ ቢደመሩ የሚሰጡን ውጤት ቁጥር ወይም ቁጥር ፲ ወይም ቁጥር ፲፫ ነውን ተብለን ብንጠየቅ መልሳችን ምንድን ነው፣ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ይሆናሉ ከተባሉት አማራጮች መካከል ምንም ዓይነት ሎጂካዊ ማስረጃ አልተገኘም። አማራጭ ቁጥሮችን ሽህ ጊዜ ብናዘዋውራቸውም እንኳ ሎጂካልየሆነው መልስ መገኘት አይችልም ለዚህ መገላገያው መልስ ባማራጮች መካከል ቁጥር ፭ ተገኝቶ ቢሆን ነበር ማለት ነው።

ሥዕላዊ/መታፎሪክ/አገላለጥ ጊዜም ቢሆን «እከሌ አባብ ነው» እከሊት ምስጥ ናት እከሌ ተኩላ ነው አነበሳ ነው እከሌ ጅብ ነው እከሊት አሞራ ናት ጭልፊት ናት/ ወዘተ/ እያልን በምንናገርበት ጊዜ ሁሉ ሎጂካዊ ምሥጢሩ ሌላ ትርጉም ያለው እንጂ እንዲሁ በጥሬ ንባብ ወይም ቃል በቃል የተባለው ሰው እነዚህን ሁሉ እንስሳት/ነገሮች/ ይመስላቸዋል ማለት አይደለም። ይህም ሁሉ የሚያስረዳን በቋንቋ ጥናትና በሥነ ጽሑፍ ዓለም ልንከተለው የሚገባንን መስመር የሚያሲዘንና ሁሉን ነገር አበጥረን አንጠርጥረን ትክክለኛውን ፈር ለማስያዝ የሚያስችለን የንግግር ጥበብ ሁሉ የሚገኘው ከሎጂክ ጥናት መሆኑን ነው ።

በሎጂካዊ አመለካከት የዐረፍተ ነገሮች አወቃቀር ዕጥር ምጥን ባለ ሁኔታ የተለያየ አዳዲስ መልክ እንዲይዝ ማድረግ ይገባል። በዓለም ከታወቁ አምስት ዋና ዋና መጽሐፍት መረዳት እንደሚቻለውም አንድ ዐረፍተ ነገር መያዝ ያለበት አማካይ የቃላት ብዛት ፲፰ አሥራ ስምንት/ ቃላት ብቻ ነው አንድ ዐረፍተ ነገር መግለጥ ያለበትም አንድ ሐሳብ ብቻ መሆን አለበት ዐረፍተ ነገር ከአንድ በላይ ሐሳብ ተሸክሞ በብዙ ቃላት ከተወሳሰበ በቀላሉ አንብቦ ለመርዳት ያዳግታል ። አጫጭር ዐረፍተ ነገሮች ግን አንባቢዎች የደረሰውን ወይም የተናገረውን ሐሳብ በቀላሉ እንዲገነዘቡት ፈጣን የማስተዋልን ጥበብ ይገልጣል ።

በሌላ በኩል አሠልቺ የሆኑ ተደጋጋሚ ዐረፍተ ነገሮች ወይም ቃላት እንዳይኖሩ ለመጠንቀቅ አንዱን ሐሳብ በተለያዩ ቃላት የመግለጥ ሎጂክ እንዲኖርም ያስፈልጋል ። ይህም ከጥንታውያኑ ኢትዮጵያውያን የቅኔ መምራን የተሠወረ እንዳልነበር የሚከተለው ቅኔ ያስረዳል ይኸውም አንዱ መምህር ቀደም ብለው» ብዙኅ ከንፍ ማዕረሩ ወኀዳጥ ሠኮና ገባሩ» በማለት የተቀኙትን ሌሎች ሁለት መምህራን በተለያየ የአነጋገር ፈሊጥ

፩—«ብዙኅ ከንፍ ማዕረረ ፍና ወኀዳጥ ገባሩ ሠኮና»

፪—«ብዙኅ ከንፍ ማዕረረ ተውላጥ ወገባሩ ሠኮና ኅዳጥ» ሲሉ በተለያየ መልክ አቅርበውት እናገኛለን። ትርጉሙም ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አዝመራ ከንፋቸው ብዙ ሆኖ ሣለ ሠራተኛው ሠኮና/እግር/ ግን አንድ ብቻ ሆነ እንደማለት ይሆናል ።

መታየት ያለበትም ዋና ቁም ነገር ተመሳሳይ ሐሳብ ያዘለውን አንድ ዓይ

ተከታዩ ወደ፳፬ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ - ግዕዝ የግዕዝ - ትምህርት

## ትምህርት ፲፪

### ቃለ እግሕ (እምሐ) የሰላምታ ቃል

መከሥት ፥— በልሳነ ግዕዝ ሦስት የተለመዱ ቃላተ እግሕ አሉ እነዚህን ቃላት ቀጥለን እንመለከታለን ። ፩ኛ— «ሰላም » የሚለው ቃል ነው ። በዚህ ቃል ሰላምታ ለመለዋወጥ « ለ » የሚለውን መስተዋ ድዳዊ ቃል በእሥሩ መራህያን አስቀድመን ግርባት አለብን ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሊተ | ለእኔ | ለነ | ለእኛ |
| ለከ | ላንተ | ለክሙ (ተባ) | ለእናንተ |
| ለኪ | ላንቺ | ለክን (አን) | » |
| ሎቱ | ለእርሱ | ሎሙ (ተባ) | ለእነርሱ |
| ላቲ | ለእርስዋ | ሎን (አን) | » |

(አሁን ሰላም ከሚለው ቃል ጋር ዓረፍተ ነገር እንሠራለን ናሁ ንጽሕፍ ዐረፍተ ነገር ምስለ ቃለ ሰላም

#### ዐረፍተ ነገር ፤

ሰላም ለከ እኁየ — ወንድሜ ሰላም ላንተ ይሁን
ሰላም ለኪ እኅትየ — እኅቴ ሰላም ላንቺ ይሁን
ሰላም ለክሙ አኃውየ — ወንድሞቼ ሰላም ለእናንተ ይሁን
ሰላም ለክን አኃትየ — እኅቶቼ ሰላም ለእናንተ ይሁን

#### ፪ኛው ቃለ እግሕ «በሐ» የሚል ቃል ነው ።

ይህንንም እንደሚከተለው እንግራለን

በሐከ እግዚእ — ጌታው እንደምን አለህ ?
በሐኪ እግዚእት — እመቤት እንደምን አለሽ
በሐክሙ አጋእዝት — ጌቶች እንደምን አላችሁ ?
በሐክን እግዝእታት — እመቤቶች እንደምን አላችሁ ?

፫ኛ ቃለ እግሕ ደግሞ « እፎ » እንዴት ከሚለው ቃል ጋር የሚሔድ ነው ። በቅድሚያ እነዚህን ቃላት

| | |
|---|---|
| እንመልከት | ግደር |
| ኃደር (ኃደርት) | መዋል |
| ውእል (ውእሎት) | መኖር |
| ሀልዎ (ሀልዎት ) | እፎ ወዐልከ |
| እፎ ኀደርከ | እፎ ወዐልኪ |
| እፎ ኀደርኪ | እፎ ወዐለ |
| እፎ ኀደረ | እፎ ወዐለት |
| እፎ ኀደረት | እፎ ወዐልክሙ |
| እፎ ኀደርክሙ | እፎ ወዐልክን |
| እፎ ኀደርክን | እፎ ወዐሉ |
| እፎ ኀደሩ | እፎ ወዐላ |
| እፎ ኀደራ | |

#### ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ የልደት ጥቅሶች

፩- እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድልጅም ትወልዳለች ፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ። ኢሳ፯፥፲፬
፪- በጨለማ የሔደ ሕዝብ ብርሃን አየ ፥ በሞት ጥላ ሀገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው ኢሳይያስ ፱ ፥ ፪
፫- ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል ። ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ። ኢሳ ፱ ፥ ፮



# ዜና ሊቃውንት

## መልአከ ሰላም ዓለምአየሁ ሻሹ

የትውልድ አገራቸው በጎጃም ክፍለ ሀገር ከደብረ ማርቆስ አጠገብ አብማ ማርያም የሆነው መልአከ ሰላም ዓለም አየሁ ሻሹ በ፲፰፻፹፬ ዓ-ም- ተወለዱ። ወደ ትምህርት ዓለም ለመሠማራት የዕድሜ ገደባቸው ሲፈ ቅድም በዚያው በተወለዱበት አካ ባቢ የንባብ ትምህርታቸውን አከ ናወኑ ።

ወዲያውም በፀዋትወ ዜማ ዋያቸው እጅግ ይታወቁና ይመሰገኑ ከነበሩት ከመሪጌታ ገብረ ሥላሴ በደብረ ማር ቆስ የዜማ ትምህርታቸውን አጠና ቅቀው ወጡ ፤ ትርጓሜ መጻሕፍት ንም ደግሞ ከመምህር ሠረገላ ፤ እን ዲሁም ከመልአከ ሰላም ገብረ ማር ያም ( ቡሬ ገብረ ማርያም ) ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ፤ ለሌሎች ለማስተማር በሚያስችል ሁኔታ በሚገባ አድር ገው ተምረዋል ።

ይልቁንም በፍትሐ ነገሥት በቁር ሉስና በሃይማኖተ አበው የትርጓሜ ስልታቸውና ይዞታቸው በሊቃው ንትም በሚጠየቁበት ጊዜ የተሠወ ረውን ምሥጢር ገልጸው በማስረ ዳታቸው ከፍተኛ የሆነ ግምት ያገ ኙበት እንደነበረ በቅርብ ያውቋቸው የነበሩት ሊቃውንት ያረጋግጣሉ ።

ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትም በፍትሐ ነገሥቱ ስለፍትሕ ሥጋዊም ሆነ ስለፍትሕ መንፈሳዊ የተጻፉ ትን አንቀጾች እንዲያስረዱዋቸው ስለሚፈቅዱ ለዘወትር እንዳይለዩ አቸው ያደርጉ እንደነበረ ይነገራል ።

ይልቁንም ከፍተኛ በሆነውጉዳይ ላይ ሁሉ ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ በመልአከ ሰላም ዓለምአየሁ ሻሹ ምክርና አስተያየት ፤ እንዲሁም በፍ ትሐ ነገሥት ትርጓሜያቸው ሒደት ይጠቀሙ እንደነበረ ታውቋል ።

ሊቱም ከዚህ ዋያቸውና ሊቅነታ ቸው የተነሣ የተወለዱበትን የአብማ ማርያም ደብር በሊቀ ጠበብትነትና በአስተዳዳሪነት ፤ የኤልያስን ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጠበብትነት ፤ በአ ለቅነት ፤ እየተዘዋወሩ እንዲያስተ ዳድሩ በየተራ ተሹመዋል ።

ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትም ከጐ ጃም ሹመት ከተሻሩ በኋላ ስለትምህ ርት አቋማቸውና በአስተያየት ረገድ ስለአበረከቱት ፍሬያማ ውጤት ቀደም ብሎ በልዩ ልዩ አቅጣጫ በተደረገው ግምገማ መሠረት ታላቁ መምህራቸው መልአከ ሰላም ገብረ ማርያም ያስተዳድሩት የነበረውን ከፍተኛውን የደንበጫ ቅዱስ ሚካኤ ልን ደብር « መልአከ ሰላም » ተብ ለው ተሾመው ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ኢትዮጵያን እስከወረረበት ጊዜ የደብሩን ካህናትና ምእመናን አስተዳድረዋል ።

ጉባኤ ዘርግተው ትርጓሜ መጻሕ ፍትንና ቅኔን በማስተማር ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አበርክተዋል ፤ ደቀመዛ ሙርቶቻቸውም በጐጃም ክፍለ ሀገር እንዲሁም በሸዋና በሌሎችም ቦታ ዎች በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግ ሎትና በማስተማር ተግባር ተሠማ ርተው ይገኛሉ ።

በጠላት ወረራ ጊዜም የኢትዮጵያን ነፃነት መታጣትና በጠላት መዳፍ ሥር መውደቅ በማስመልከት አዘው ትረው የሚያፈሱት ዕንባና ያደርጉት የነበረው ልባዊ ኀዘን ተሰምቶባ ቸዋል ። ያገራችሁን ጥፋት በዳመነ ገጽታ ለምን ትመለከታላችሁ ይል በነበረው ዕውር ጠላት ዘንድ ልዩ ልዩ ፈተና እንደደረሰባቸው ይነ ገራል ።

በዚህ ዓይነቱ የሥቃይ ሕልውና ላይ ሳሉም በእግዚአብሔር ኃይ ልና በኢትዮጵያ አርበኞች አንድ ነት የተገኘውን የነፃነት ፋና ለማየት ዕድል ሳያገኙ በ፲፱፻፴፪ ዓ- ም- የካ ቲት ፮ ቀን በድንገተኛ ሕመም፯ምክ ንያት አርፈው በዚያው በተወለዱበት በአብማ ማርያም ደብር ሥርዓተ ቀብ ራቸው ተፈጽሟል ።

መልአከ ሰላም ዓለምአየሁ ሻሹ በቅኔ ዋያቸው እጅግ የታወቁና የተ መሰገኑ ስለነበሩ በተሾሙባቸው አድ ባራት ብቻ ሳይሆን ፤ በሌሎቹም የጐጃም አብያተ ክርስቲያናት ቅኔ እንዲያበረክቱ በየጊዜው ጥሪ ይደር ሳቸው ነበር ።

ለመረጃም ያህል ከብዙዎቹ ቅኔ ዎቻቸው አንዱ ከዚህ ቀጥሎ የተመ ለከተው ነው ።

### መ ወ ድ ስ

ረከበ ሳእል እንተ ኢሐለየ ፤ ቅብዓ ዘይት ቅዱስ ወእክሊለ መንግሥት ከመ ይንግሥ እዕዱጊሁ ዘጠፍኡ እንዚ የኀሥሥ አምጣነ ልማዱ ለአ ምላክነ ውሂብ ዘኢተሐለየ ውስቴታ ለከርሥ ፤

ሆሣዕናሁሰ ለጴጥሮስ ለኃሢሠ ክልኤ እዕዱግ እመ ምድረ ሳሌም ይገይሥ ።

ረከበ በፈቃዱ ፈቃደ ሥሉስ ቅዱስ
ወሪቀ ምራቅ ሀየንተ ቅብዐ ወሀ
የንተ አክሊል ተኰርአ ርእስ ።
ወኢይጽሕቅ ቅብዓተ ለከዊነ
ንጉሥ ሐዲስ ።
አምጣነ ንጉሥ ቅድመ
ዓለም ወቅብዐ ዘይቄድስ ።



www.ethiopianorthodox.org

# መልካሙን የምሥራች እንናገር

«ዛሬ የምሥራች ቀን ነው እኛም ዝም ብለን እስኪነጋም ድረስ ብን ቆይ በደለኞች እንሆናለን ኑ እንሂድ እንናገር ተባባሉ» ይህ ጥቅስ የሚገኘው መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ፯-፱ ላይ ነው ። ይህንንም ቃል የተናገሩት አራት ለምጻሞች ሲሆኑ የሶርያው ንጉሥ ወልደ አዴር ሠራዊቱን ሁሉ ሰብስቦ የእስራኤል ከተማ የሆነችውን ሰማርያን በከበባትና የሰማርያም ሕዝብ ዙሪያዋን በግንብ በታጠረችው በሰማርያ ከተማ ውስጥ ሆነው በታላቅ ረኀብና ችግር ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ነው ። ሕዝቡ የሚቀምሰው የሚል ሰው ስለሌለው ከረኀቡ የተነሳ የአህያ ራስ በአምሳ ብር ፣ የርግብ ኩስ በአምስት ብር እስከ መሸጥ ደርሶ ነበር ፣ በኋላም እርሱም ጠፍቶ ሰው ሰውን እንደ እንጀራ አሳምጦ እስከ መብላት በመድረሱ እናት ልጅዋን እስከ መብላት የደረሰችበት ጊዜ ነበር።

በዚህን ጊዜ ነበር እነዚህ ለምጻሞች መልካሙን የምሥራች እስኪ ነጋ ድረስ ዝም ብንል በደለኞች እንሆናለን ብለው የተማከሩት ። የምሥራቹም እግዚአብሔር ሕዝቤን ከዚህ ከታላቅ ረኀብ ይታደግ ዘንድ በዙሪያቸው የከበቡአቸውን የሶርያውን ሠራዊት የሰረገላና የፈረስ የብዙም ጭፍራ ድምፅ ስለአሰማቸው ፍርሃትና ድንጋጤ ወድቆባቸው ስለነበር ነፍሳቸውን ብቻ ለማዳን ሁሉን ትተው በመሸሻቸው እግዚአብሔር የማረከውን ምርኮ ሕዝቡ እንዲከፋፈልና ከዚህ በታላቅ ምርኮ ሕዝቡ ከረሃብና እርስ በእርሱ ከመበላላት እንዲድን የሚያበስር ነበር ።

አዎን እስኪነጋ ድረስ ይህንን የምሥራች ሳይነግሩ ቢዘገዩ በደለኞች ናቸው ፣ የበደልም ቅጣት አለው ። ታሪኩ በዝርዝር በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ በምዕራፍ ፮ና በምዕራፍ ፯ ላይ ተገልጾአል ።

ዛሬስ በታላቅ መንፈሳዊ ረሃብና ጥማት ላይ ለሚገኘው ሕዝብ መልካሙን የምሥራች ቃለ ወንጌልን መናገር አይገባንም ? ዛሬም የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች በታላቅ መንፈሳዊ ረሃብ ላይ አይገኙምን ? ከመንፈሳዊው ረሃብ የተነሳ ፍቅር አልቀዘቀዘችምን ? ስለ ዚህስ እርስ በእርሱ መበላላት መተማማት ፣ መጨቃጨቅ ከቤተክርስቲያን ውስጥ ጀምሮ የለምን ? የሰይጣን ጆሮ አይስማው እንጂ ስንት ጉድ አለ ? ይህ ሁሉ ስለምን ሆነ ቢሉ ወንጌል አልተሰበከችማ ?

በጴጥ ፩ ፣ ፰ እንዲህ ይላል «ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጐ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና» በማለት ያብራራል ። የእግዚአብሔር ሕዝብ በጠላቶቻቸው በሶርያውያን እንደተከበቡ ሁሉ ዛሬም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሚያስገነዝበን ባላጋራችን ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ቤተሰቦች ዙሪያ እየዞረ የእግዚአብሔርን መንጋ ለመንጠቅ እንዳደባ ነው የሚያስጠነቅቀን ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ዲያብሎስን በመስቀሉ ሥር ቀጥቅጦ ታላቅ ምርኮን ማርኮአል ፣ የዘላለም ሕይወትን ፣ የመንፈስ ፍሬን «ፍቅር ፣ ደስታ ፣ ሰላም ፣ ትዕግሥት ቸርነት ፣ በጎነት . . . ወዘተ » ገላ ፭፳፪ የመሳሰሉትን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ ለእግዚአብሔር ቤተሰቦች ተዘጋጅቶአል ። «ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታ ሰጠ» ኤፌ ፬፣፰ ታዲያ ይህንን ታላቅ ምርኮ ታላቅ የምሥራች ነው ለእግዚአብሔር ቤተሰብ የምንናገረው እንናገር ዘንድ ኃላፊነት አለብን ባንናገር ግን ታላቅ በደል ነው ። ስለዚህም ነው ብንዘገይ እንኳን በደለኞች እንሆናለንና ኑ እንሂድ የምሥራቹን እንናገር የተባባሉት ፤ ዛሬም እኛ ነገ ዛሬ ሳንል ለስብከተ ወንጌል እንነሳ ።

ይኸንንም በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኃይል የተገኘውን ምርኮ ነው ። የምሥራች ብለን የምንናገረው ይኸን ብናደርግ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ከታላቅ መንፈሳዊ ረኀብና ጥማት ይድናሉ እኛም ታላቅ በረከትን ከእግዚአብሔር እንቀበላለን ። ግን ብንዘገይ ለስብከተ ወንጌል ቸልተኞነት ቢኖረን እንደተጠቀ ሰው በደለኞች ሆነን እንገኛለን ።

ከዲ. አረጋይ ደመቀ
ደብረ ገሊላ አማኑኤል

# የድርሰት አጻጻፍ...

ከ፳፩ኛው ገጽ የዞረ ፤

ነት ሐሳብ ምሥጢራዊ ታሪኩን ሳይለውጡ ሶስት የቅኔ መምህራን ቤት የሚመቱባቸውን ሶስት ፊደሎች በመቀያየር በሶስት ዓይነት መንገድ እንዴት ለማቅረብ እንደቻሉ ማጤን ነው።

ሌላው ማስገንዘቢያ ዐረፍተ ነገሮች ማጠር አለባቸው ሲባል ደግሞ ሊገልጡት የሚገባውን አንድ ሐሳብ ሳይዙ እንደዝናም ጠብታ /ነጠብጣብ/ ዓይነት ቁርጥ ቁርጥ የሚሉ የሕፃናት አፍ መፍቻ ዓይነት መሆንም የለባቸውም በጣም ሳይረዝም እጅግ ሳያጥር አንድን ሐሳብ በትክክል ለመግለጥ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው ማለት ነው።

አንድን ሐሳብ በተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ስለመግለጥ ሌላ አንድ ምሳሌ እንሆ።

«መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ተሐውጽ ከመ ጎሕ»

፩—እንደንጋት ፀሐይ የምትፈልቅ ያች ማን ናት ?

፪—ማን ናት ይህች የንጋት ፀሐይ የምትመስል ?

፫—እንደንጋት ፀሐይ የምታበራ ይህች ማን መሆንዋ ነው? ስለ ሐሳብ አወቃቀር ሎጂክ ከሞላ ጐደል የቀሠምነውን ጠቃሚ ሐሳብ እዚህ ላይ እንደምድምና በተከታዩ እትም የሥርዓተ አንቀጽና የድርሰት አካል አከፋፈል ሕግን እንመረምራለን። ስለሎጂክ ጥናት ሰፋ ያለ ሐሳብ ለማግኘትም በዶ/ር የማነ ገብረ ማርያም የተጻፈ የፍልስፍና ትምህርት ቅጽ፪የተሠኘውን ማንበብ እንደሚጠቅም እያሳሰብን ስለአቀራረባችን ያላችሁንም አስተያየት እንድትለግሱን አደራ እንላለን።

ቄ/መክብብ አጥናው



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ :

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ :

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየ ተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገለግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት :

የስልክ ቁ. 11
የመልእክት ሣ. ቁ.
አዲስ አበባ :

www.ethiopianorthodox.org